# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

ሰዋስው
ቃላት
መፃፍ
ሥነ-ጽሑፍ
መናገር
ማንበብ
ማዳመጥ

## ፬ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# ማሳሰቢያ

## ለመፅሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ!

የመማሪያ መፅሀፋችሁ የትምህርት ቤቱ ንብረት ቢሆንም እንደራሳችሁ ንብረት መያዝ ይኖርባችኋል። እንዳይጠፋም ጥንቃቄ አድርጉ።

1. መፅሀፉን በቀላሉ እንዳይበላሽ በጠንካራ ወረቀት ሽፍኑት
2. መፅሐፉን ደረቅና ቆሻሻ በሌለበት ቦታ አስቀምጡት።
3. መፅሀፉን ለመጠቀም ስትፈልጉ እጃችሁን አፅዱ።
4. በመፅሀፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ በፍፁም አትፃፉ፤ ስዕሎችንም አትሳሉ።
5. ለመፅሀፉ ገፅ መለያ ወይም እልባት ስትፈልጉ ጠንካራ ወረቀት ወይም ክር ተጠቀሙ እንጂ ገፁን አትጠፉ።
6. በመፅሀፍ ውስጥ ያሉትን ገልፆች ወይም ስዕሎች ገንጥላችሁ አታውጡ።
7. የመፅሀፉ ሽፋን ወይም ገፅ ከተገነጠለ በማስትሽ አያይዙ።
8. መፅኀፉ ቦርሳ ውስጥ ሲገባና ሲወጣ እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ።
9. መፅሀፉን ለሌላ ሰው ስታውሱም ሆነ ስትዋሱ እንዳይቀደድ ጥንቃቄ አድርጉ።
10. መፅሀፉን ስትገልጡት ሽፋንና ገፁ እንዳይገነጣጠል መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡ። ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት።

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 6 ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 6ኛ ክፍል

አዘጋጆች:-

ሰለሞን ከበደ (MA)
ዝናሽ በፍቃዱ (B.Ed)
ድሪባ ሩሹ ( MA)

ገምጋሚዎች:-

ለዝና መንግስቴ(B.Ed)
ነፃነት ጥጋቡ (MA)
ይሻሙ ጌራወርቅ(MA)

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

**ምዕራፍ አንድ፡- ሀገር በቀል ባህል**-----------------------------------------------1

**ምዕራፍ ሁለት፡- ተላላፊ በሽታዎች**-----------------------------------------------14

**ምዕራፍ ሶስት፡- ግጥም**--------------------------------------------------------28

**ምዕራፍ አራት፡- ቴክኖሎጂ**-----------------------------------------------------43

**ምዕራፍ አምስት፡- ግብር ለሀገር ዕድገት** -----------------------------------55

**ምዕራፍ ስድስት፡- ስኬት**-------------------------------------------------------72

**ምዕራፍ ሰባት፡- የሕይወት ታሪክ**--------------------------------------------87

**ምዕራፍ ስምንት፡- የአየር ንብረት**-------------------------------------------100

**ዋቢ መፃሕፍት**------------------------------------------------------------114

## መግቢያ

የአማርኛ ቋንቋ ትህምርት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስድስተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በስምንት ምዕራፍ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ማጎልበት፣ የስነ ጽሁፍንና የሰዋስው እውቀትን ማዳበር ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎችን በመርሃ ትምህርቱ ላይ በግልጽ ሰፍረው ይታያሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል አንዱ የተማሪዉ የመማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ ይህ መጽሀፍ ደግሞ በየጊዜው የሚሻሻልባቸው ምክንያት ውስጥ አንዱ የመርሃ ትምህርቱን ዓላማዎች በማስፈጸም ረገድ የመጽሀፉን አቅም በማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁለተኛው ደግሞ መርሃ ትምህርቱ ላይ ማሻሻያ ወይም ለዉጥ ሲደረግ ነው፡፡

ይህ የስድስተኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሆነበት በ2013 ዓ.ም መርሃ ትምህርቱ እንዲሻሻል በመደረጉ ነው፡፡ በዚህ መፅሀፍ መርሃ ትምህርቱ ትኩረት የተሰጠባቸው ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹ፣ ማብራሪያዎቹ፣ ተግባራቱ፣ መርሃ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በክሂልና በእውቀት ዘርፍ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ በየምዕራፉ ማብቂያ የማጠቃለያ ሀሳብ ከመቅረቡም በላይ የክለሳ ጥያቄዎችና ተማሪዎች ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘጋጅተዋል፡፡

በመጨረሻም ለመፅሀፉ ዝግጅት ፅሁፎቻቸውን ያዋሱንን ሁሉ እያመሰገንን ስለ መፅሀፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀርቡ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ሀገር በቀል ባህል

### የምዕራፉ ዓላማዎች፡-

**ተማሪዎች! ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ካዳመጣችሁት ዉስጥ የተረዳችሁትን ትዘረዝራላችሁ ፡፡
- ስለራሳችሁ ባህልና ልምድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ሀሳብን በነፃነትና በፍጥነት አፍልቃችሁ በማስፋፋት ትናገራላችሁ፡፡
- በምንባቡ መሰረት ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡
- ከቃል ግንድ ቅድመ እና ድህረ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ቀላል ፈሊጣዊ ንግግሮችን ትጠቀማላችሁ፡

## ክፍል አንድ፡-ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

1/ መምህራችሁ “ጥበብን ፈልጎ ስለማግኘት” በሚል ርዕስ የቀረበዉን ምንባብ ሲያነቡላችሁ በጥሞና ተከታተሉ፡፡

2/ የሚነበበዉን ምንባብ እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

3/ ከመዘገባችሁት ማስታወሻ ላይ የተረዳችሁትን ሀሳብ ተነጋገሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ/ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በፊት ከምታውቁት ነገር ሀሳባችሁን በነፃነት በማፍለቅ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. ከዚህ ቀደም የሰማችሁት በአካባቢያችሁ በጉዲፈቻ እያሳደጓቸው ካሉት ሰዎች ስለ ጉዲፈቻ የተገነዘባችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
2. በጉዲፈቻ የሚያድጉ ልጆች የሚያገኙት ጥቅምና ጉዳት ተናገሩ፡፡

ለ/ መምህሩ/ሯ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን “ቁሳዊ ባህል” የሚል ምንባብ አዳምጣችሁ በመልዕክቱ ላይ ተወያዩበት፤ የደረሳችሁበትንም ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

ሀ/ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡-

1. ጉዲፈቻ ምንድን ነዉ?
2. ጉዲፈቻ በማንና በማን መካከል ይከናወናል?
3. በጉዲፈቻ ዉስጥ ስንት አይነት የአስተዳደግ ስርዓቶች አሉ?

## ጉዲፈቻ

ጉዲፈቻ በሰጪና በተቀባይ መካከል በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚከወን በመሆኑ የሁለት ተወቃሪ አካላት መኖር ግድ ይላል፡፡ ተወቃሪ አካላቱ ዝቅ ሲል የተቀባይና የሰጪ ቤተሰቦች ከፍሲልም የሁለቱን ጎሳዎች ይመለከታል ስለሆነም የትግበራዉ መሰረት የተወቃሪ አካላት መኖር ነዉ ፡፡ ጉዲፈቻ የኦሮሞነት አንድ መገለጫ እንደመሆኑ አፈጻጸሙ በእምነት እና በማህበራዊነት መርሆች ላይ የተመሰረተ ጥብቅ ክዋኔ ነዉ፡፡

በኦሮሞ ባህል ወደሚተገበረዉ ጉዲፈቻ በቀጥታ ከመግባቴ በፊት በኦሮሞ የልጆች አስተዳደግን በተመለከተ ጥቂት ሀሳብ ልሰንዝር ፡፡ የኦሮሞ ባህልና ቱርዝም ኮሚሽን፤እንደሚገልጸዉ በኦሮሞ የኦሮሞ የልጆች ማሳደግ “ኢልማ ቆይራ” Ilmaa qoyiraa በሚል መጠሪያ እዉቅና የተሰጣቸዉ 3 አይነት የልጅ አሰተዳደግ ሰርአቶች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. በሞጋሳ ስርዓት ወደ ኦሮሞ ጎሳነት ተለዉጦ የአንድ ቤተሰብ  የኦሮሞ ልጅነት የተሰጠዉ “ኢልማ በርጩማ “ይባላል፡፡
ለ. ገና እንደ ተወለደ የተጣለን ልጅ ከተጣለበት ስፈራ በማንሳት ያሳደጉት ልጅ “ኢልማ ሚጢ”ይባላል፡፡ ሚጢ በኦሮሞ ባህል የወንድነት መለያ ሲሆን አንድ የኦሮሞ ልጅ እንደተወለደ ከወንድ ብልቱ ከፍ ብሎ ከእንብርቱ ደግሞ ወረድ ብሎ የሚገኝ ስፍራ በወገብ ዙርያ የሚታሰር ዶቃ የተደረገበት ቀጭን ቆዳ ነዉ፡፡

ሌላዉ የልጅ አይነት "ኢልማ ዴይራ" ይባላል፡፡ በጥሬዉ ትርጉሙ ዲቃላ ልጅ እንደ ማለት ነዉ፡፡ እናቱ በአባትና እናቷ ቤት እያለች ወይም ከጋብቻ ዉጪ የተወለደ ልጅ ሲሆን በእናቱ አባት ስም ይጠራል፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሦሥቱ የልጅ ዓይነቶች በጥቅሉ "ኢልማ ቆይራ"/ Ilma qoyiraa/
ይባላል፡፡ከኦሮሞ ባህል አኳያ በባሌ ዞን የሚተገበሩ ሦስት አይነት የልጅ መቀበል ስርዓቶች አሉ፡፡
አንደኛዉ የጉዲፈቻ አይነት "ኢልማ አኮታ" የሚባለዉ ሲሆን አንዲት
ሴት እህቷ ጋር ትሄድና ከልጆችሽ መካከል አንዱን ስጪኝና ላሳድግ ብላ ስትጠይቅ የተጠየቀችዉን ልጇን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነችበትን አዎንታዊ ምላሽ ነዉ፡፡

ሁለተኛዉ አንድ ሰዉ ከሞተ በኋላ በ40ኛ ቀን በመቃብሩ ላይ የድንጋይ ሀዉልት ለማስቀመጥ የሚችል ወንድ ልጅ የለሌዉ ከሆነ በስርዓቱ ላይ የተሰበሰቡ ጎሳዎች ከሌላ ጎሳ ትልቅም ቢሆን ወንድ ልጅ የሚጠየቅበትና የተጠየቀዉም ጎሳ የፈቀደበት ክዋኔ ሲሆን "ኢልማ ሶዱ" ይባላል፡፡ እነዚህ ሁለቱ የልጅ ቅብብሎሽ ህጋዊነት የሌላቸዉ ከመሆናቸዉም አንፃር የተሰጡትም ልጆች ወደ ወላጆቻቸዉ ተመልሶ መሄድ ቢፈልጉም ከልካይ የለባቸውም፡፡ ሦስተኛዉ ግን በብዙ ስርዓት ታጅቦ የሚሰጥ ለህጋዊነቱ ማረጋገጫ ያለዉ፣ ጥብቅ በሆነ ልማዳዊ ባህል የሚተገበርና ሲወራረስ የመታዉን ባህል የተከተለ "ጉዲፈቻ ገያ" የሚባለዉ ነዉ፡፡ "ገያ" ህጋዊ መሰረት ያለዉ የጉዲፈቻ አይነት ነዉ፡፡"ገያ" የሚባለዉ የጉዲፈቻ አሰጣጥ ከመተግበሩ በፊት የወደፊት አሳዳጊዎቹ ለልጁ ማዘያ የሚሆን በደንብ የለሰለሰ አንቀልባ "Baattoo" ያዘጋጃሉ፡፡ በተጨማሪም የወተት መያዣ ጡጦም የሚያዘጋጁ ሲሆን ጡጦዉንም በጨሌና በጠፍር ጥብጣብ (saamsaa) በደንብ ያስኬዱታል፡፡ ልማዳዊ መተዳደሪያ መሰረት አድርጎ በጉዲፈቻነት የሚሰጠዉ ልጅ ወደ አሳዳጊዎቹ የሚተላለፈዉ በተወለደ ከ1 እስከ 2 ወራት እድሜ ዉስጥ ነዉ፡፡ህፃኑ በዚህ ወላጆቹን ያዉቃል ተብሎ ስለማይገመት አሳዳጊው ዘንድ ተረጋግቶ ያድጋል፡፡ እያደገ በሄደም ቁጥር ወላጆቹን ለይቶ ስለማያዉቅ የስነልቦና ጫና የለበትም ተብሎ ይታመናል፡፡
(ምንጭ፡- የምረቃንናየእርግማን ክዋኔና ፋይዳ በባሌ ኦሮሞ በአበበ መርዕድ ፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያየቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ 2003ዓ.ም (አ.አ.ዩ)

## ተግባር አንድ

### ሀ/ የሚከተሉትን ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነዉን "እዉነት" ትክክል ያልሆነዉን ደግሞ "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ጉዲፈቻ በሰጪና በተቀባይ መካከል በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚከወን ስርዓት ነዉ፡፡

2. ጉዲፈቻ የኦሮሞነት አንዱ መገለጫ ባህል ነዉ፡፡
3. በሞጋሳ ስርዓት ወደ ኦሮሞ ጎሳነት ተለዉጦ የአንድ ቤተሰብ የኦሮሞ ልጅነት የተሰጠዉ "ኢልማ በርጬማ" ይባላል፡፡
4. ከጠቃሚ ባህሎች ዉስጥ አንዱ የሴት ልጅ ግርዛት ነዉ፡፡
5. "ኢልማ ሚጢ" ማለት ጥሬ ትርጉሙ ዲቃላ ማለት ነዉ፡፡
6. ጉዲፈቻ በእምነትና በማህበራዊነት መርሆች ላይ የሚመሰረት ክዋኔ ነዉ፡፡
7. ጉዲፈቻ በጎጂ ባህል ዉስጥ ይመደባል፡፡

ለ/ በምንባቡ መሰረት ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ በመምረጥ መልሺ/ስ፡፡

1. ከኦሮሞ ባህል አኳያ በባሌ ዞን የሚተገበሩ ስንት አይነት የልጅ መቀበል ስርዓቶች አሉ?
   - ሀ/ ሁለት
   - ለ/ ሦስት
   - ሐ/ አራት
   - መ/ ስድስት
2. ሲወራረስ ሲል ምን ማለቱ ነዉ?
   - ሀ/ ሲቀባበል
   - ለ/ ሲነካካ
   - ሐ/ ሲያያዝ
   - መ/ ሲቀመጥ
3. "ኢልማ ሶዱ" የየትኛዉ የኦሮሞ ባህል ጉዲፈቻ ነዉ?
   - ሀ/ ሀረር
   - ለ/ ጅማ
   - ሐ/ ሸዋ
   - መ/ ባሌ
4. ታጅቦ ሲል፡- ሀ/ ተከቦ ለ/ ተሰብስቦ ሐ/ ተበትኖ መ/ ተስቦ
5. በምንባቡ መሰረት ህጋዊ መሰረት ያለዉ የጉዲፈቻ አይነት ምን በመባል ይታወቃል?
   ሀ/ ኢልማ ቆይራ ለ/ ዴይራ ሐ/ ገያ መ/ መልስ የለዉም

**ማስታወሻ**

የቃላት አዉዳዊ ፍቺ ማለት፡- አንድ ቃል በዓረፍተ-ነገር አገባቡ መሰረት ወይም ዙሪያ ገብ ንባብ ማለት ነዉ፡፡

ምሳሌ፡- ልጁ በአስተሳሰቡ በሰለ፡፡ ( በአዕምሮ መጎልመሱን)፡፡

በቆሎዉ ቶሎ በሰለ፡፡ ( ለመብል ደረሰ)፡፡

ሐ/ ከዚህ በታች ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አገባባዊ ፍቻቸዉን ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- አንቀልባ- የህጻን ማዘያ

ሀ. ሚጢ---------------

ለ. ክዋኔ----------------

ሐ. መገለጫ------------

መ. ተወቃሪ------------

ሠ. እንብርት-----------

መ/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸዉ፡፡

1. የባህልን ምንነትና ጥቅሞችን ዘርዝሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ ስለሚፈፀሙ ጎጂና ጠቃሚ ባህሎችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. በትምህርት ቤት ቅጥር ሆነ በአካባቢያችሁ ያሉትን ማስታወቂያዎች አንብባችሁ የተረዳችሁትን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡
4. ባህልና የባህል መገለጫዎች ላይ በቡድን ተወያዩበት፡፡

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### የማስታወቂያ አፃፃፍ

- ማስታወቂያ ማለት፡- አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ ሌላዉ ህብረተሰብ እንዲያዉቅለት የሚፈልገዉን ነገር በፅሁፍ ማሳወቅ ነዉ፡፡

### የማስታወቂያ አፃፃፍ መመሪያ

ቁጥር-----------

ቀን--------------

ቦታ---------

አድራሻና ጊዜ---------

ተፈላጊ ችሎታ ወይም ጉዳይ------------

ማስታወቂያዉን ያዘጋጀዉ አካል ፊርማ እና ማህተም ወዘተ. ናቸዉ፡፡

## ተግባር አንድ

ሀ/ በተናጠል ወይም በግል የቀን ዉሎአችሁን ፃፉና ከቡድን አጋሮቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

ለ/ ከላይ ስለ ማስታወቂያ አፃፃፍ በተማራችሁት መሰረት የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ወክላችሁ የቅጥር ማስታወቂያ በመፃፍ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

## ተግባር አንድ

ሀ/ የሚከተሉት ቃላት ሆሄያቱ ቦታ ተቀያይሯል፤ ሆሄያቱን አስተካክላችሁ ቃል መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ቀረሰ = ሰረቀ

በለሰ = ለበሰ/ ሰለበ

1. በለደ =
2. መጀረ =
3. በረሸ =
4. ደደቀ =
5. ረደበ =
6. መጥጠ =
7. መጥረ =
8. ደገአ =
9. ሰለፈ =
10. ረየቀ =

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## 1. ቅጥያ

ቅጥያዎች በዋና ቃል ላይ ወይም በንግግር ክፍል ላይ ተደርበዉ ብዙ ቁጥርን፣ ባለንብረትነትን፣ ፆታን፣ መደብን፣ ወገንን፣ አይነትን፣ ወዘተ. የሚያመለክቱ ናቸዉ፡፡

### ሀ. ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎች፡-

ብዙ ቁጥር የሚያመለክቱ ቅጥያዎች በስም ላይ ተደርበዉ ይገባሉ፡፡ እነርሱም፡- -ዎች፣ -ኦች፣ -ዋት፣ -ኣት፣ ወዘተ. ናቸዉ፡፡
ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን በዋና ቃል ላይ አጣምሮ ወይም ነጥሎ መፃፍ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡-

| በመነጠል | በማጣመር |
|---|---|
| ሰዉ-ኦች | ሰዎች |
| ልጅ-ኡ | ልጁ |
| በሬ-ዎች | በሬዎች |
| ቃል -ኣት | ቃላት |
| ዶሮ-ዎች | ዶሮዎች |
| እፅ-ዋት | እፅዋት |

## ተግባር አንድ

ሀ/ ከሚከተሉት ቃላት ዋና ቃልና ቅጥያዎች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

| ቃል | ዋና ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- እየሄደ | ሄደ | እየ- |
| እንደሰራች | ሰራ | እንደ-/ -ች |
| 1. አልመጣ | ------------------ | ------------------ |
| 2. በላህ | ------------------ | ------------------ |
| 3. መጣችሁ | ------------------ | ------------------ |
| 4. ተከፈለ | ------------------ | ------------------ |

5. ቤቱ ------------------ ------------------
6. ፈጣኖች ------------------ ------------------
7. መታቸው ------------------ ------------------
8. ቤትህ ------------------ ------------------
9. ተከፈለ ------------------ ------------------
10. ተስማማሽ ------------------ ------------------
11. ሆዳም ------------------ ------------------
12. እየሰራ ------------------ ------------------
13. መጣላችሁ ------------------ ------------------
14. ልጅዎ ------------------ ------------------
15. በላክ ------------------ ------------------

## ክፍል ሰባት፡- ሥነ -ጽሁፍ

**ፈሊጣዊ አነጋገር**

ፈሊጣዊ አነጋገር ማለት፡-ቃላት ቀድሞ የነበራቸዉን ትርጉም በማስፋት የሚያገለግሉ ከሆነ ፈሊጣዊ አነጋገር ይባላል፡፡ ፈሊጣዊ አነጋገሮች የአንድ ቃል ወይም የሁለት ቃላት ጥምረት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡-ሂያጅ በምንልበት ጊዜ ቀደም ሲል የነበረዉ እና በብዙዎች የሚታወቀዉ ፍቺ ተጓዥ የሚል ነዉ፡፡ ትርጉሙ ሰፍቶ “አመንዝራ” የሚል ተጨማሪ ፍቺ ይይዛል፡፡

የአንድን ሰዉ የሀዘን ስሜት ለማሳወቅ ”ሰዉየዉ በጣም አዘነ“ ከማለት ይልቅ

“ሰዉየዉ ልቡ ተሰበረ” ተብሎ ቢገለጽ የሚያስተላልፈዉ መልዕክት የሀዘኑን ሁኔታ አክብዶ የሚገልጽ ይሆናል፡፡

### ተግባር አንድ

**ሀ/ ከዚህ በታች ለቀረቡት ፈሊጣዊ አነጋገር በቀረበዉ ምሳሌ መሰረት ስሩ፡፡**

ለምሳሌ፡-

- ✓ ሁለት ልብ ----ወላዋይ
- ✓ ብቅል አዉራጅ --በጣም ረጅም

1. ቅቤ አንጓች -----------------
2. ቅጠል በጣሽ-----------------
3. በሬ ወለደ -------------------

4. ስጋዬ ------------------
5. ቦጨቀ ------------------
6. ህገ-ወጥ ------------------
7. ሆድና ጀርባ ------------------
8. ለዕውቀት በቃ------------------
9. ልበ-ጡል ------------------
10. መሚጠጫ ------------------
11. መሸጦ ------------------
12. ስድ ------------------
13. ልበ-ሙት ------------------
14. ባላንጣ ------------------
15. ቆሌ-ቢስ ------------------

ለ/ ለሚከተሉት ፈሊጣዊ ንግግሮች ትክክለኛዉን አባባል የያዘዉን ሆሄ ምረጡ፡

1. የዉሃ ሽታ ሆነ
   ሀ/ ተወደደ ለ/ ደብዛዉ ጠፋ
   ሐ/ ጥሩ ሽታ ያለዉ መ/ መጥፎ ሽታ ያለዉ
2. አይኗን ቀቅላ የበላች
   ሀ/ አይናፋር ለ/ ተሽኮርማሚ
   ሐ/ የማትፈራ መ/ ሀሞተ-ቢስ
3. ጥርሱን ነከሰ
   ሀ/ አቄመ ለ/ ሳቀ
   ሐ/ ተቆረቆረ መ/ ተገረመ
4. ስማ-በለዉ
   ሀ/ አዋጅ ለ/ ተረጋግተሽ
   ሐ/ አታስጨንቀዉ መ/ አለሁ በለዉ
5. ኑሮዋ ከእጅ ወደ አፍ ነዉ፡፡
   ሀ/ የሞላት ለ/ የተትረፈረፋት
   ሐ/ የእለት ጉርስ ብቻ ያላት መ/ የአመት ጉርስ ብቻ ያላት
6. ዉሃ አጣጭ
   ሀ/ የማይጠቅም ጓደኛ ለ/ የኑሮ ጓደኛ
   ሐ/ የትምህርት ቤት ጓደኛ መ/ ጠላት

7. የበግ ለምድ የለበሰ

ሀ/ አስመሳይ ለ/ ተንኮለኛ

ሐ/ የበግ እረኛ መ/ ሀቀኛ

8. ፍርድ ቀጠነ

ሀ/ ፍርድ ተጓደለ ለ/ ፍርድ ተዛባ

ሐ/ ፍርድ ተዋሀደ መ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸዉ

9. የጥርስ ስጋ

ሀ/ ጨቅጫቃ ለ/ ተጫዋች

ሐ/ ሀሜተኛ መ/ የዋህ

10. ግንባሩን አስመታ

ሀ/ ተጎዳ ለ/ ደጅ ጠና

ሐ/ ግንባሩ ተመታ መ/ ጠፋ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የጉዲፈቻ ምንነትና የልጅ አስተዳደግ ስርዓቶችን ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሰረት ጉዲፈቻ በሰጪና በተቀባይ መካከል በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ሊከወን እንደሚችልና በተጨማሪም በሁለት የተለያዩ ጎሳዎች መካከል ሊፈፀም እንደሚችል ተመልክተናል፡፡ ጉዲፈቻ የራስ ያልሆነን ልጅ ወስዶ እንደ ራስ አድርጎ ማሳደግን የሚመለከት የቆየ የኦሮሞነት ትልቁ የባህል መገለጫ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል የማስታወቂያ አፃፃፍ መመሪያን ተከትለን እንዴት ማስታወቂያ መጻፍ እንደምንችል አይተናል፡፡ እንዲሁም የቅጥያ ምንነት፣ቅጥያ ብዙ ቁጥርን፣ፆታን፣ባለንብረትነትን እንዴት እንደሚያመላክት ተመልክተናል፡፡

በመጨረሻም የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ምንነት አንስተን እንዴት መተርጎም እንደምንችል ተመልክተናል፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጉዲፈቻ ምን ምን ጥቅሞች አሉት?
2. ባህል በስንት ይከፈላል? ምሳሌ ስጡ::
3. የማስታወቂያ አፃፃፍ መመሪያን በቅደም ተከተል ዘርዝሩ::

- ከዚህ በታች የቀረቡትን ፈሊጣዊ ንግግሮች ትረጉም ስጡ፡፡
  1. እጅና ጓንት ሆኑ-------------------
  2. ሆደ ሰፊ --------------------
  3. የደም ገንቦ--------------------
  4. ምራቋን የዋጠች-------------------
  5. ጆሮ ጠቢ -------------------
  6. እግር ጣላት--------------------

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ጉዲፈቻ ባህል የቀረበውን ምንባብ ይዘት መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የማስታወቂያ አፃፃፍ መመሪያን መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ስለ ቅጥያ ምንነት መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ስለ ፈሊጣዊ አነጋገር ምንነት መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ተላላፊ በሽታዎች

### የምዕራፉ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- ቀጥተኛ የሆኑ ጥያቄዎችን አዳምጣችሁ በቃል ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- ከዝርዉ ፅሁፍ ለወጡ ቃላት ትርጉም ለመስጠት ታነባላችሁ።
- በርከት ያሉ ስርዓተ-ነጥቦችን በፅሁፍ ዉስጥ ትጠቀማላችሁ።
- ቃላትን በዓረፍተ-ነገር ዉሰጥ በትክክለኛዉ ትገለገላላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህራችሁ "ኤድስ" በሚል ርዕስ ከመምህሩ መምሪያ ሶስት ጊዜ ያነቡላችኋል፡፡ ግጥሙን ከማዳመጣችሁ በፊት ከርዕሱ በመነሳት የርዕሱ ትኩረት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ፡፡

ለ/ ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ከመምህሩ መምሪያ ምንባብ የወጡ ናቸዉ፡፡ ግጥሙ ሲነበብላችሁ በጥሞና አዳምጣችሁ ተመሳሳይ ፍቻቸዉን ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- መዛመት - መሰራጨት

አስደናቂ - አስገራሚ

1. ባላንጣ ------------------
2. አጥፊ ------------------
3. ተጠምቶ ------------------
5. ወገን ------------------
6. ገደብ ------------------
7. ነጥሎ ------------------
8. ሕግ ------------------
9. ፈጀ ------------------

## ክፍል ሁለት ፡-መናገር

### ተግባር አንድ

1. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ከተላላፊ በሽታዎች ስለ ኤድስ የሚያነቡላችሁን አድምጣችሁ የመፍትሄ ሀሳቡ ላይ ተነጋገሩበት፡፡
2. በአካባብያችሁ ያሉትን የተለያዩ የጤና ባለሙያዎችን በመጠየቅ ስለተላላፊ በሽታዎችና መከላከያ መንገዶችን በመጠየቅ በክፍል ዉስጥ ተነጋገሩበት፡፡
3. የወረርሽኝ በሽታን ያለክትባት የምንከላከልበት ነገሮችን ወላጆቻችሁን በመጠየቅ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

## ክፍል ሦስት :- ማንበብ

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ከተላላፊ በሽታዎች መካከል የሚታዉቁትን ጥቀሱ::
2. ኮቪድ- 19 ምን አይነት በሽታ ነዉ?
3. የኮቪድ-19 መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን ዘርዝሩ::

ኮቪድ-19



ከዚህ ቀደም ከነበረው ጊዜ በተለይ በአሁኑ ወቅት ዓለም በወረርሽኝ ተጨንቃ
ትገኛለች:: በርካቶች ወረርሽኙን ለማስወገድ በሚያስችል ክትባት ላይ ተስፋቸውን ጥለው እየተጠባበቁ ቢሆንም፤ አያት ቅድመ አያቶቻችንን አጋጥሟቸው የነበሩት አብዛኞቹ በሽታዎች አሁን ድረስ ከሰው ልጅ ጋር አብረው አሉ::
በዚህ ባለንበት ዘመን አዲስ አይነት የሳርስ ኮሮናቫይረስ ስጋት ዓለምን አጋጥሟታል:: ይህ ቫይረስ ኮቪድ-19 የተባለውን የመተንፈሻ አካላት ላይ በሽታን የሚያስከትል ነው::
ሳርስ-ኮቪድ-2 ተብሎ የሚታወቀው ኮሮናቫይረስ ቀደም ብሎ ከተከሰተው የወጣ ሲሆን በሽታዎችን በሚያጠኑ ባለሙያዎች ዘንድ ለየት ያለ እንደሆነ ይነገራል:: በበሽታው በአንዳንዶች ላይ ምንም ምልክት የማያሳይ ሲሆን በሌሎች ላይ ደግሞ እጅግ አደገኛ ሊሆን ይችላል:: ምልክቶቹን በማያሳዩ ሰዎች አማካይነትም በከፍተኛ ደረጃ ከሰው ወደ ሰው የመዛመት አቅም አለው:: "በዚህም ምክንያት በብዙ ቦታዎች ላይ ለመቆጣጠር ሳይቻል ቀርቷል" ይላሉ ፕሮፌሰር ሪሌ::
እስካሁን ድረስ በመላው ዓለም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎች በወረርሽኙ ሰበብ የሞቱ ሲሆን፤ ቁጥሩም ከዚህ በላይ ከፍ ሊል እንደሚችል ተሰግቷል:: አዲሱ የኮሮናቫይረስ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ገድሏል:: በዓለም ዙሪያ ለኮሮናቫይረስ መከላከያ ክትባትና ውጤታማ ህክምና ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ቢሆንም የበሽታው ስጋት በአብዛኛው የምድራችን ሕዝብ ዘንድ አሳሳቢ ሆኖ ቀጥሏል::

በአሁኑ ጊዜ ዓለም ላይ እየተከሰቱ ካሉና በቫይረስና በባክቴሪያ አማካይነት ከሚመጡ በሽታዎችመካከል ኮሮና ቫይረስ አንዱ ነው። በሰው ልጅ ታሪክ ትልቁ የሚባለው ወረርሽኝ በጊዜ ሂደት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ገድለዋል። የዓለም ሕዝብ ቁጥር ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል። የሕዝብ ቁጥር አነስተኛ ቢሆን ኖሮ በቀደመው ዘመን የነበሩት ወረርሽኞች የሚያደርሱት ጉዳት እጅግ ከፍ ያለ ይሆን ነበር።


ቀደም ሲል የተከሰቱትን ወረርሽኞች በመቆጣጠር በኩል፤ የበሽታዎቹን መተላለፊያ መንገዶች በተመለከተ ያለው ዕውቀት መጨመሩ፣ የሕብረተሰብ ጤና ግንዛቤ ዘመቻዎች፣ አዳዲስ ህክምናዎችና ክትባቶች ወሳኝ ሚና ነበራቸው። አሁን ዓለምን እያስጨነቃት ያለው የኮሮናቫይረስንም ለመቆጣጠር ከላይ የተጠቀሱት አይነት የተቀናጁ እርምጃዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። "አስተማማኝና ውጤታማ" ክትባት የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ እንዲያበቃ የሚያስችል ቢሆንም፤ ፕሮፌሰር ሪሌ እንደሚሉት ግን ውጤታማ ክትባት መቼ እንደሚገኝ "በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም።"

ከዚያ ይልቅ ግን በሂደት ተፈጥሯዊ በሽታውን የመቋቋሚያ አቅምን በማዳበር ከኮቪድ-19 ጋር አብረን መኖርን ልንለማመድ እንችላለን። "በእርግጠኝነት በአምስት ዓመት ወይም ከዚያም ባጠረ ጊዜ ውስጥ በዓለም ዙሪያ ጥቅም ላይ የሚውል በጣም ጥሩ የተባለ ክትባት እናገኛለን፤ ወይም ከበሽታው ጋር ለረጅም ጊዜ ከመቆየት የተነሳ በቂ ተፈጥሯዊ መከላከያን በማዳበር በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱ ትንንሽ የኮቪድ-19 ወረርሽኞችን በመቋቋም ከወረርሽኙ ጋር አብረን መኖርን እንለምዳለን" ይላሉ ፕሮፌሰር ሪሌ።

ከምድር ላይ የጠፋው የፈንጣጣ በሽታ እንደሚያረጋግጠው፤ የዓለማችን የሳይንስ ማኅበረሰብ በአንድነት በበሽታው ዙሪያ መስራት ከቻለ አስደናቂ ውጤቶች ይገኛሉ። አዲሱ የኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ በከፍተኛ ደረጃ ምልክት ሳያሳዩ በሽታውን የሚያስተላልፉ ሰዎች ስላሉት በሽታውን ለመቆጣጠር በጣም ፈታኝ ቢሆንም፤ ፕሮፌሰር ሪሌ ግን ለበሽታው መፍትሄ ለማግኘት በዓለም ደረጃ የሚደረገው "አስደናቂ" ጥረት ውጤታማ እንደሚሆን ተስፋ አላቸው።

“በኮሮናቫይረስ ዙሪያ እንደሚደረገው ጥረት አይነት የጋራ ሥራ በዓለም ላይ ከዚህ በፊት ታይቶ አይታወቅም” ይላሉ። “ይህም በቅርቡ የጋራ ስኬት እንደሚሆን ተስፋ አለኝ።” በተጨማሪም የኮሮናቫይረስ ከዚህ በፊት የዓለምን ማኅበረሰብ የፈጁት አብዛኞቹ ወረርሽኞች አሁንም በዙሪያችን እንዳሉ እንድናስታውስ ያደርገናል። እነዚህ ሚሊዮኖችን የገደሉ ወረርሽኞች ሲያበቁም፤ የበሽታዎቹ ምክንያት የሆኑት ቫይረሶቹና ባክቴሪያዎች እንዲሁም ያስከተሉት ህመም በታሪክነት አብሮን ይኖራል።

(ምንጭ፡ የኢምፔሪያል ኮሌጅ ኦፍ ለንደን ፕሮፌሰር ስቴቨን ሪሌ እና የዓለም ጤና ድርጅት :-ከሚል ፅሁፍ ለመማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተወሰደ)።



## ተግባር አንድ

**ሀ/ ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን በማንበብ ትክክል የሆነዉን ሀሳብ እዉነት ትክክል ያልሆነዉን ደግሞ ሀሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡**

1. የኮቪድ-19 ቫይረስ በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ ነዉ፡፡
2. የኮቪድ-19ን ፕሮቶኮል በመጠበቅ በሽታዉን መከላከል ይቻላል፡፡
3. የኮቪድ-19 ቫይረስን ለመከላከል ማስክ ማድረግ ብቻ በቂ ነዉ፡፡
4. የኮቪድ-19 ቫይረስ በአሁኑ ሰዓት እጅግ ብዙ ሰዎችን እያጠቃ ይገኛል፡፡
5. እድሜና ፆታ ከማይለዩ በሽታዎች አንዱ የኮቪድ-19 ቫይረስ በሽታ ነዉ፡፡
6. የኮቪድ-19 ቫይረስ ህፃናትን እንጂ አዛዉንቶችን አያጠቃም፡፡

**ለ/ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ቃላት በምንባቡ መሰረት ተቃራኒ ፍቻቸዉን ፈልጉ፡፡**

ምሳሌ፡- ስኬት- ውድቀት

1. መዛመት -------------------
2. ስጋት -----------------------
3. ተፈጥሮአዊ ---------------
4. በአንድነት ------------------
5. ማህበራዊ ------------------
6. ብዙ -------------------------
7. ወረርሽኝ -------------------
8. ከፍአለ ----------------------
9. የቀድሞ ---------------------
10. ታማሚ ---------------------

ሐ/ ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቻቸዉን ከሰጣችሁ በኋላ አረፍተነገር ስሩባቸዉ፡፡

ምሳሌ፡- ፈታኝ- አስቸጋሪ

❖ በ2013 ዓ.ም ፈታኝ ጊዜን አሳልፈናል፡፡

1. ዕውቀት ----------------------------------------------------
2. ማስወገድ --------------------------------------------------
3. በሽታ -------------------------------------------------------
4. ሚና ---------------------------------------------------------
5. ምክንያት ---------------------------------------------------

## ክፍል አራት፡-መፃፍ

1. ስርዓተ-ነጥቦች

➢ **ስርዓተ-ነጥብ ማለት**፡- በፅሁፍ ውስጥ ማስተላለፍ የተፈለገዉን ሀሳብ በትክክል መረዳት የሚስችሉ የጋራ መግባቢያ ምልክቶች ናቸዉ፡፡

በአብዛኛዉም በአገልግሎት ላይ ካሉት ስርዓተ-ነጥቦች ዉስጥ ጥቂቱን ቀጥለን እንመለከታለን፡-

1. አንድ ነጥብ ( . )

አንድ ነጥብ አንዳንዴ "ይዘት" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን በሶስት የተለያየ መልክ ያገለግላል፡፡

1.1 ቃላትን በምህፃረ ቃል አሳጥሮ ለመፃፍ የሚያገለግል ሲሆን ሁለት የተለያዩ ስርዓቶችን ይከተላል፡፡

ሀ/ የቃላትን መነሻ ፊደል ብቻ በመዉሰድ

ምሳሌ፡- ኦ.ል.ማ (የኦሮሚያ ልማት ማህበር)
አ.አ.ዩ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

ለ/ የአንድን ቃል መነሻና መድረሻ ሆሄ ብቻ በመዉሰድ

ምሳሌ፡- ወ.ር (ወታደር)

ዶ.ር (ዶክተር)

1.2 ብርና ሳንቲሞችን እንዲሁም ሙሉና ክፍልፋይ ቁጥሮችን ለመለየት

ምሳሌ፡- 6.30ብር (ስድስት ብር ከሰላሳ ሳንቲም)

3.9 (ሁለት ነጥብ ዘጠኝ)

2.45 (ሁለት ነጥብ አራት አምስት)

## 2. ሕዝባር ( / )

2.1 ቀን፣ ወርና ዓመተ-ምህረትን ለያይቶ ለመፃፍና ለማንበብ ይረዳል፡፡

ምሳሌ፡- 14/11/2013ዓ.ም

2.2 ቃላትንና ሀረጋትን አሳጥሮ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ዓረፍተ-ነገር (ዓ/ነገር)

ወይዘሪት (ወ/ት)

መምህር (መ/ር )

## 3/ ሁለት ነጥብ (፡)

ሁለት ነጥብ ቃላት በእጅ ፅሁፈት ላይ ከመጠን በላይ ተቀራርቦ አንባቢዉን እንዳያስቸግሩ ወይም ፊደላት ከቃል ክፍላቸዉ ርቀዉ ወደ ሌላኛዉ ቃል በመጠጋት እንዳያደናግሩ በቃላት መካከል በመግባት ድንበር ሆኖ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- 1. አበበ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ሄደ፡፡

2. 2፡00 ( ሁለት ሰዓት)

## ተግባር አንድ፡-

### ሀ/ በሚከተለዉ አንቀፅ ዉስጥ ሊገቡ የሚገባቸዉን ስርዓተ-ነጥቦች በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረት መልሺ/ስ፡፡

ምሁራን እንዲህ ብለዋል ከማይምነት ያልተላቀቀ ህብረተሰብ በአመራረቱ በአኗኗሩ በአስተሳሰቡ ኋላ ቀር ነዉ በተፈጥሮ ከመገልገል ይልቅ ለሷ እጁን ይሰጣል

1. ምሁራን . . . በሚለዉ አንቀፅ የጥቅስ ምልክት የት ይገባል?
   ሀ/ "ከማይምነት . . . ይሰጣል፡፡"
   ለ/ "ምሁራን.... ይሰጣል"፡፡
   ሐ/ "በአመራረቱ . . . ነዉ፡፡"
   መ/ "በአመራረቱ... ይሰጣል"፡፡
2. ከላይ በቀረበዉ አንቀፅ ድርብ ሰረዝ የት ይገባል?
   ሀ/ ህብረተ-ሰብ፤
   ለ/ ይሰጣል፤
   ሐ/ ብለዋል፤
   መ/ የትም አይገኝም
3. በአንቀፁ ዉስጥ ነጠላ ሰረዝን የት ቦታ እንገለገላለን?
   ሀ/ በአመራረቱ፣ . . . አኗኗሩ፣ . . . በአስተሳሰቡ፣ በሚሉት ቦታዎች
   ለ/ በአመራረቱ፣ . . . በአኗኗሩ፣ በሚሉት ቦታዎች
   ሐ/ በአመራረቱ፣ ከሚለዉ ቃል ቀጥሎ
   መ/ በአስተሳሰቡ፣ ከሚለዉ ቃል ቀጥሎ
4. ምሁራን . . . በሚለዉ አንቀፅ አራት ነጥብ የት ይገባል?
   ሀ/ ብለዋል፡፡ . . . ይሰጣል
   ለ/ ብለዋል፡፡ . . . ኋላ ቀር ነዉ፡፡ . . . ይሰጣል፡፡
   ሐ/ ብለዋል፡፡ . . . ኋላ ቀር ነዉ፡፡
   መ/ ኋላ ቀር ነዉ፡፡. . . ይሰጣል፡፡

### ለ/ በሳጥን ዉስጥ ከቀረቡት ስርዓተ-ነጥቦች መካከል በመምረጥ በክፍት ቦታዎቹ ላይ በማስገባት ደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፡፡ | " " | ፤ | |
| ፣ | ? | | |

1. እናቴ ከገበያ ሙዝ-------ብርትኳን -------ማንጎ------አፕልና አቮካዶ ከገበያ ገዝታ መጣች፡፡
2. ዝናቡ ሊዘንብ ነዉ-------ስለዚህ ወደ ቤቴ መሄድ አለብኝ፡፡
3. የገዳ መምህራችን-------ነገ ፈተና አላችሁ እንዳትቀሩ-----አሉ፡፡
4. አያንቱ የት ሄደች-------
5. ደን ሲጨፈጨፍ መሬት ይራቆታል------

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች ከቀረቡት ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በመውሰድና በማቀናጀት ከአስር ያላነሰ ቃላትን መስርቱ፡፡

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ና | ሳ | ል | ቀ | ኛ | ፅ | ጅ | ም |
| ሬ | ኒ | ለ | ጥ | ደ | ሀ | ማ | ት | ያ |
| መ | ቡ | ብ | ር | ሻ | ህ | ላ | ሸ | ፀ |
| ው | በ | ስ | ድ | ተ | ን | ቸ | ፊ | ጀ |

ምሳሌ፡- ጅማ
ስኒ
ጥብስ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ

ሀ/ በሚከተሉት ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ ተስማሚ ስርዓተ-ነጥቦችን በተገቢው ቦታ አስገብታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ስምህ ማን ነው

- ✓ ስምህ ማን ነው?

1. አልማዝ መቼ መጣች
2. ጠዋት ጠዋት ቁርስ መብላት አልወድም

3. ተማሪዎች ነገ ፈተና ስለምትፈተኑ አጥኑ
4. መገርቱ ለእናቷ ልብስ ምግብ የሚጠጣ ውሃ ይዛ መጣች
5. ዛሬ እለቱ ምንድን ነው
6. ፈተናው ደረሰ ስለዚህ ማጥናት አለብኝ
7. አያቶቻችን እድሜ መስታወት ነው አሉ
8. አቤት ወጣቱ በኮቪድ በሽታ አለቀ
9. ጫላ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ መፅሀፍ ድብተር እርሳስ እስክብርቶ ላጲስ እና ማስመሪያ ይዞ ነው

10.የቶሎሳ ልጅ ሰኔ 10 2013 ዓም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ተወለደ

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህሩ/ሯ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ተረት አዳምጡና ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ለቀረበው ተረት ርዕስ መሆን የሚችለው የቱ ነው?
   - ሀ/ መስማት የሚችል ቤተሰብ
   - ለ/ መስማት የተሳነው ቤተሰብ
   - ሐ/ መስማማት የቻለው ቤተሰብ
   - መ/ መስማማት ያልቻለው ቤተሰብ
2. በተረቱ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት?
   - ሀ/ ሰው የሚሰማው ያዳመጠውን ነገር ነው፡፡
   - ለ/ ሰው የሚናገረው ሲያናግሩት ነው፡፡
   - ሐ/ ሰው የሚሰማው መስማት የሚፈልገውን ብቻ ነው፡፡
   - መ/ ሰዎች ቤተሰቦቻቸውን አለማዳመጣቸውን ነው፡፡
3. በተረቱ ውስጥ ያሉት ቤተሰብ------------------ናቸው፡፡
   - ሀ/ አባት፣ አክስት፣ እናት
   - ለ/ አጎት፣ አያት፣ እህት
   - ሐ/ ወንድም፣ እህት፣ አባት
   - መ/ አባት፣ ሴት ልጅ፣ እናት
4. ከሚከተሉት መካከል በተረቱ ውስጥ የተጠቀሱት እንስሳት የትኞቹ ናቸው/
   - ሀ/ አህያ፣ ከብቶች፣ ዶሮዎች
   - ለ/ አህያና ከብቶች
   - ሐ/ ውሻ፣ ፈረስ፣ ድመት
   - መ/ አህያ፣ ፈረስ፣ ዶሮ፣ ድመት

5. በምንባቡ መሰረት አህያው፡

   ሀ/ ይሸጣል ለ/ አይሸጥም

   ሐ/ ተሸጧል መ/ አይታወቅም

6. መስማት የተሳነው ሰው ወደ ወንዝ ውሃ ሊያጠጣ የሄደው------ነው፡፡

   ሀ/ ጥጃውን ለ/ በሬውን

   ሐ/ አህያውን መ/ ላሙን

7. የሴት ልጃቸው የትዳር ሁኔታ------------ነው፡፡

   ሀ/ ያገባች ለ/ ያላገባች

   ሐ/ አግብታ የፈታች መ/ መልስ የለውም

8. መስማት ከተሳነው ሰውዬና ከእረኞቹ ቀድሞ ውሃ ያጠጣው ማን ነው?

   ሀ/ እረኞቹ ለ/ ማስማት የተሳነው ሰውዬ

   ሐ/ ሁለቱም አላጠጡም መ/ ሀ ና ለ መልስ ናቸው

9. መስማት የተሳናቸው ቤተሰብ ብዛት-----------ናቸው፡፡

   ሀ/ አምስት ለ/ አራት

   ሐ/ ሶስት መ/ ሁለት

10. መስማት የተሳናቸው ቤተሰብ የመኖሪያ አካባቢ የት ነው?

   ሀ/ ከተማ ለ/ ገጠር

   ሐ/ አይታወቅም መ/ ሀ ና ለ መልስ ናቸው

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ከተላላፊ በሽታዎች አንዱ የሆነውን የኮቪድ-19 ቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን በስፋት ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሰረት የኮቪድ-19 ቫይረስ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍበት መንገድ በትንፋሽ፣በንኪኪና የተለያዩ እንቅስቃሴ በምናደርግበት ጊዜ የጥንቃቄ ጉድለት በሚያጋጥመን ጊዜ ለቫይረሱ ልንጋለጥ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡- ማክስ አለማድረግ፣ሳኒታይዘር አለመጠቀምና እጅን በአግባቡ በሳሙናና በውሃ በደንብ አለመታጠብ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የኮቪድ-19 ቫይረስ መከላከያ መንገዶች፡- ርቀትን መጠበቅ፣ማክስ ማድረግ፣ሳንታይዘር መጠቀም፣አለአግባብ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን መቀነስ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡

በሌላ በኩል ስለ ቃላት ፍቺ ባነሳንባቸው ክፍሎች ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የሚንሰጠው በገቡበት አውድ እንደሆነ አይተናል፡፡ በተጨማሪም በስርዓተ-ነጥቦች ስር የአንድነጥብ፣ ሁለትነጥብ፣ድርብሰረዝ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ህዝባር፣አራት ነጥብ፣የጥያቄ ምልክት ተግባራትን ተመልክተናል፡፡ ተገቢው ማብራሪያና ምሳሌዎች ተሰጥቶታል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. የኮቪድ-19 ቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡
3. የስርዓተ-ነጥቦችን ምንነትና ተግባራትን ግለፁ፡፡

- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ፈልጉላቸው፡፡
    1. ህልም
    2. ጨዋ
    3. ግብረ ገብ
    4. ፈጣን
    5. ደፋር
    6. ድንቁርና
    7. አቀበት
    8. ሌጣ
    9. ነፃነት
    10. ኖረ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✔ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ተላላፊ በሽታዎች ኮቪድ የቀረበውን ምንባብ ይዘት መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4 | የስርዓተ-ነጥብ ምንነትን በሚገባ መግለጽ እችላለሁ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## ግጥም

### የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች:-

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ቀላል ትዕዛዞችን አዳምጣችሁ ግልጽ ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሰረት በማድረግ በቃል ትመልሳላችሁ ።
- በቡድን ዉይይት ላይ ትሳተፋላችሁ ።
- የምንባቡን ሀሳብ ለመገመት ርዕሱን ታነባላችሁ ።
- በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተጻፈዉን ቀላል ማስታወሻ በትክክል ትፅፋላችሁ ያዳመጣችሁትን ቃላት ተረድታችሁ ትጠቀማላችሁ።
- የግጥም ሙያዊ ቃላትን ትዘረዝራላችሁ፡

## ክፍል አንድ፡-ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ “ክፋት” በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም ሲያነቡላችሁ በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ በግጥሙ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ “እዉነት” ትክክል ካልሆኑ ደግሞ “ሀሰት” እያላችሁ በቃል መልሱ፡፡

1. እንደ ገጣሚዉ አባባል ሰዉ ተንኮለኛ መሆን የሚጀምረዉ በእግሩ መሄድ ሲጀምር ነዉ፡፡
2. በምንባቡ መሰረት የሰዉ ልጅ ልብስን ለብሶ ይወለዳል፡፡
3. ባዳመጣችሁት ፅሁፍ ሰዉ ካደገ በኋላ የተመሰለዉ በተኩላ ነዉ፡፡
4. ገጣሚዉ እንደ ተምሳሌት የተጠቀማቸዉ ተኩላና በግን ነዉ፡፡
5. በግጥሙ ዉስጥ ሊተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት ሰዉ ሲወለድ የዋህ መሆኑንና ሲያድግ ክፋትን መማሩ ነዉ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ሴቷ( ክፍል አንድ)

ማህፀን አንጣፊ-ያሳብ ዘር አርጋፊ፣
የታሪክ አተላ-ዝቃጭ ድፍዳፊ፡፡
ከሆነ ወንዱ ግንድ- አካል አምሳሉን ከጅ፣
የነፈገ እህቱን- ያለ ድርሻዉ ወሳጅ፣
ብሶት ለዘመናት- በልጅ ላይ ፈራጅ፣
እናቱን አዋራጅ- አይወለድ ዉራጅ፡፡
እናት መንታላዋ- ባተሌ በማጀት፣
ዉብ እምቦቀቅላ- ብርቅዬዋ ልጅ ናት፣
እህት አበባዋ- ጎጂ ባህል የጎዳት፣
ለባሏ ዘዉድ ናት- ለምን ክብር ነሷት፡፡
ሁሉ ደግነቷ -ስራ ወዳድ ነሽ፣
የሺ ባለጉዳይ- አስተማሪ ነሽ፡፡

### ተግባር አንድ

ሀ/ ግጥሙን መሰረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ሴት በማህበረሰቡ ዉስጥ ምን ምን አስተዋጽኦ ታበረክታለች ?
2. ግጥም የሚነበብበት ስልት ከስድ(ዝርዉ) ፅሁፍ የተለየ ነዉ? ተወያዩበት፡፡
3. በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሴቶች በምን በምን ስራዎች ላይ ይሳተፋሉ?

ለ/ ሴቷ የሚል ግጥም ሲነበብ በጥሞና በማድመጥ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

1. ግጥሙ ሲነበብ ካዳመጣችሁት መካከል አንኳር አንኳር መልዕክቶችን ተናገሩ፡፡
2. ግጥሙ ስለ ማን ያወራል?
3. በግጥሙ ዉስጥ የፆታ እኩልነትን የሚያንፀባርቅ ስንኝ አለ? ካለ ጠቁሙ፡፡
4. ይህን ግጥም ካዳመጣችሁ በኋላ ከአካባቢያችሁ ማህበራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ነገር አለዉ? ተናገሩ::

ሐ/ ግጥሙን መሰረት በማድረግ ከአምስት ያልበለጡ አረፍተነገሮችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ሴት የሺ ባለጉዳይ አስተማሪ ነች፡፡

2. ሴት ለባሏ ዘውድ ናት፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### ሴቷ( ክፍል ሁለት)

አካሏ አካላችን - ቆራርጠን ከትብቷ ፣
ተካፍለናት ቅርጫ- ጎጆ ማስወጣቷ፣
ሲሆን መረሳቷ- ድምፅ ማሰማቷ፣
ከወንድ አቻነቷ- አይቀሬ ነዉ ሴቷ፡፡
መብት ከማሳወቅ- ማንፌስቶ ባሻገር፣
በልማት ተሳትፎ- በከተማ ገጠር፣
ወስና በስልጣን- ሀብትን ትቆጣጠር፡፡
በነፃነት መንፈስ - ተደራጅታ ትንቃ፣
የበታችነቷን - አስተሳሰብ ፍቃ፡፡
የባህል ጠባሳዉ- ፆታ አድሎ ከንቱነት፣
ተገፎ ይነሳ- በሴቷ- አርበኝነት፣
ራዕይዋ እዉን ሆኖ- ትበይን ሹመናት፣
የማራኪነት ዙፋን -ተጎናፅፋ እንያት፡፡

(ምንጭ፡ ከረምርም ሀብታሙ "ይህም የኛ ሰዉ ነዉ" ከሚል በ2001ዓ.ም ከታተመ የግጥም መድብል የተወሰደ)፡፡

ተመሳሳይ ቃላት

1/ ተመሳሳይ ቃል ማለት፡- በፍቺ ወይም በትርጉም ከተሰጠዉ ቃል ጋር የሚመሳሰል ወይም የሚገናኝ ማለት ነዉ፡፡

ለምሳሌ፡- መልካም- ጥሩ

ለማ- ዳበረ

ሀቅ- እዉነት

ሁከት- ብጥብጥ

ሰም- የማር ገፈት

ሰንጋ- በደንብ የተቀለበ ከብት

ሻረ- ተወ

ቁጭት - ፀፀት

## ተግባር አንድ

ሀ/ በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ከምንባቡ ለወጡት ቃላት ተመሳሳያቸዉን በ "ለ" ስር ከተዘረዘሩት ቃላት ምረጪ/ጥ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቅርጫ | ሀ/ ተቋቋመ |
| 2. ጎጆ | ለ/ ቤት፣ ትዳር |
| 3. ፍቃ | ሐ/ እኩያ |
| 4. አድሎ | መ/ መከፋፈል |
| 5. ተደራጀ | ሠ/ አመለካከት |
| 6. ተጎናፀፈ | ረ/ ሰርዛ |
| 7. አቻ | ሰ/ ተላበሰ |
| 8. ተገፎ | ሸ/ ተራቁቶ |
| 9. ራዕይ | ቀ/ ዓላማ |
| 10. አስተሳሰብ | በ/ ማበላለጥ |

# ክፍል አራት፡- መፃፍ

## አያያዥ ቃላት

አያያዥ ቃላት ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀርግ፣ አረፍተነገርን ከአረፍተ ነገሮች ጋር ለማያያዝ ወይም ለማቆራኘት ያገለግላል፡፡ በዚህም የተሟላ ሀሳብ ያስተላልፋሉ፡፡

የአያያዥ አይነቶች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹን እንመልከት፡-

እና(ና)፣ ወይም፣ ግን፣ ይሁን እንጂ፣ ደግሞ፣ ስለዚህ፣ በተጨማሪ፣ እንዲሁም፣ ወዘተ. ናቸዉ፡፡

- ምሳሌ፡- ዮዲትና አስፋዉ መጡ፡፡
- ዳንዲ በትምህርቱ ጎበዝ በመሆኑ መምህራን ይወዱታል፡፡
- የሂሳብ ትምህርትን በጣም እወዳለሁ፤ ይሁን እንጂ አይገባኝም፡፡

## ተግባር አንድ

ሀ/ የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| እና | ስለዚህ | አለበለዚያ | ወይም |
| ይሁን እንጂ | ቢሆንም | | |
| ነገር ግን | ምክንያቱም | በኋላ | እናም |
| ከዚያም | ሆኖም | | |

ምሳሌ፡- ለልጄ ጫማ <u>ወይም</u> ልብስ መግዛት አለብኝ፡፡

1. ኮኬት---------ሄኖክ መጡ፡፡
2. ሰለሞን በጣም ታሟል-----------ወደ ሀኪም ቤት መሄድ አለበት፡፡
3. የእንግሊዝኛ ትምህርትን በጣም እወዳለሁ---------አይገባኝም፡፡

4. ዮናታን ዛሬ መጥቶ ነበር-------ከኬራጅ ጋር አልተገናኙም፡፡
5. ሰኚ ሁልጊዜ ያጠናል፤ --------በፈተና ጥሩ ዉጤት አያመጣም፡፡
6. በቅድሚያ ዳንዲ መጣ--------ዓለሙ ተከትሎት መጣ፡፡
7. ከትምህርት ቤት አትቅር፤--------የእለቱ ትምህርት ያመልጥሃል፡፡
8. የቤት ስራ ሰርቻለሁ፤-----------በክፍል ዉስጥ እሳተፋለሁ፡፡
9. የቤት ዉስጥ ስራ በዝቶብኛል፤----------ባለኝ ጊዜ አጠናለሁ፡፡
10. ኳስ መጫወት እወዳለሁ፤-----------እንድጫወት አይፈቀድልኝም፡፡

ለ/ የሚከተሉትን አንቀፅ አያያዥ ቃላት በመጠቀም አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ዘወትር ጠዋት ጠዋት ከመኝታችን ስንነሳ ፊታችንን መታጠብ 1____ጥርሳችንን መፋቅ ይኖርብናል፡፡ ምግብ ከመመገባችንም ሆነ ከተመገብን 2_______ እጃችንን መታጠብ መዘንጋት የለብንም 3______ ያልታጠብን እንደሆነ ለጤናችን ጠንቅ 4---------- ጥንቃቄ ያስፈልገናል፡፡ 5 ----------- ሌላ ሰዉ እስኪነግረን ድረስ ሳንጠብቅ የሰዉነታችንና የፀጉራችንን ንፅህና መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ 6------------ አቅማችን የሚፈቅደዉን ስራ መስራት መለማመድ ይገባል፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ-ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ከፈለ

- ወንድሜ የቤቱን ክራይ በወቅቱ ከፈለ፡፡

1. ለመለመ
2. ጅረት
3. በቀለ
4. ተጓዘ
5. ስንሰለት
6. ህልም
7. እድል

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

1. አረፍተነገር

   1.1 የዓረፍተነገር ምስረታ

የተለያዩ ሆሄያት በአንድ ላይ ተቀናጅተዉ ቃላትን ይሰጡናል፡፡ የተለያዩ ቃላት ደግሞ ሀረግን ይሰጡናል፡፡ ሀረጎች ተዋህደዉ ዓረፍተነገር ይመሰርታሉ፡፡ ዓረፍተነገር ደግሞ የተሟላ ሀሳብን ያስተላልፋል፡፡

   1.2 የዓረፍተነገር ዓይነቶች፡-

ዓረፍተነገር በያዘዉ የግስ መጠን ነጠላና ዉስብስብ ዓረፍተነገር በማለት መመደብ ይቻላል፡፡

ሀ/ ነጠላ ዓረፍተ-ነገር፡- ነጠላ ዓረፍተነገር የሚባለዉ በአንድ ዓረፍተነገር ዉስጥ አንድ ግስ ብቻ ያለዉ ነዉ፡፡

ምሳሌ፡-

- ሕፃን ልጅ ወተት ይወዳል፡፡
- ያ ልጅ ጎበዝ ተማሪ ነዉ፡፡

ለ/ ዉስብስብ ዓረፍተነገር፡- ዉስብስብ ዓረፍተነገር የሚባለዉ ከአንድ ግስ በላይ በዓረፍተነገር ዉስጥ ሲኖር ዉስብስብ አረፍተነገር ይባላል፡፡

ምሳሌ፡-

- ሲፈን እናቷ ከጅማ ስለመጣች ተደሰተች፡፡
- ሰለሞን ምግቡን እንደበላ ተኛ፡፡

## ተግባር አንድ

### ሀ/ ቀጥለዉ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች “ነጠላ” ወይም “ውስብስብ“ አረፍተ ነገር በማለት መልሺ/ስ፡፡

1/ ገንዘብ እንደ ተላከልኝ ወደ ባንክ ሄድኩ፡፡-------------

2/ አዲስ ብርጭቆዉን ሰበረች፡፡-----------------

3/ ከትምህርት ቤት በመቅረቴ ፈተና አመለጠኝ፡፡-----------

4/ ኬትም እናቷን ትመስላለች፡፡-------------

5/ ተማሪዎች ከክፍል በመዉጣታቸዉ መምህሩ ተናደደ፡፡---------------

6/ ሔለን ያሬድ መኪና እንደገዛ ሰማች፡፡------------------

7/ ዱሬቲ ድሪባ ወደ መቀሌ ስለሄደ አለቀሰች፡፡-----------------

8/ እሱ ወታደር ሆነ፡፡------------------

# ክፍል ሰባት፡- ስነ-ጹሁፍ

1. ስነ-ግጥም

የስንኞች መድረሻ ሆሄያትን ቤት እያስመቱ መናገር ግጥም ይባላል፡፡

1.1 የግጥም ሙያዊ ቃላት

1.1.1 ስንኝ፡- ስንኝ ማለት የግጥም አንድ መስመር ተሳክቶ ሲያበቃ ስንኝ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- አይዞህ የእኔ ጌታ ነገርህን አትርሳ ( ስንኝ)1

አለስልስህ ዝራ የስንዴዉን ማሳ ( ስንኝ) 2

ይህ ግጥም ሁለት ስንኞች አሉት፡፡

1.1.2 ሀረግ፡- ሀረግ ማለት የስንኝ ግማሽ ወይም በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የቃላት ስብስብ ሀረግ ይባላል፡፡

ምሳሌ፡- እምቢልታ መለከት / የሚሰማዉ የት ነዉ፣ (ስንኝ) 1

ሀረግ አንድ ሀረግ ሁለት

አንዱም በስርቆሽ በር/ አንዱም በግቢ ነዉ፡፡ (ስንኝ) 2

ሀረግ ሶስት ሀረግ አራት

## የእምባ ሽለቆ

መከራ ተረግዞ ተወልዶ ችግር፣

ሥቃይ ተሞሽራ ሲዘፈን ባገር፣

ኃዘን ስትዘፍን አታሞ ስትመታ፣

ድህነት ሲሽልል እየነፋ እምቢልታ፡፡

ረሃብ ሲያቅራራ በጣለዉ ሰለባ፣

ቀጠና ደረሰ ድምፁን እያስተጋባ፡፡

ቡትትም አጊጣ ከዲሪቶ ጋራ፣

ዝተትና ማቅም ሆነዉ በየተራ፡፡

መጡ ከእኔ ዘንዳ አብሮኝ ሊኖሩ፣

ተስማምተዉ ደረሱ እየተባበሩ፡፡

ምንጭ፡ ከብርሃኑ ገበየሁ “የአማርኛ ስነ-ግጥም” ከ2003ዓ.ም እትም የተወሰደ)፡፡

## ተግባር አንድ

ሀ/ ከላይ የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ፊደል በመምረጥ መልሺ/ስ፡፡

1. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

   ሀ/ 8 ለ/ 16

   ሐ/ 10 መ/ 4

2. ግጥሙ በስንት ሀረጎች ተዋቀረ?

   ሀ/ 9 ለ/ 20

   ሐ/ 19 መ/ 12

3. በስንኝ ሦስት ዉስጥ "አታሞ" የሚለዉ ቃል ፍቺዉ፡-

   ሀ/ አስታኮ ለ/ ታሞ

   ሐ/ ከበሮ መ/ አስታማሚ

4. "ቡትትም <u>አጊጣ</u> ከዲሪቶ ጋራ" የተሰመረበትን ቃል ሊተካ የሚችል የቱ ነዉ?

   ሀ/ ተዉባ ለ/ ተላጭታ

   ሐ/ ፉንጋ ሆና መ/ ቆሽሻ

5. "መጡ ከእኔ ዘንዳ አብሮኝ ሊኖሩ" የሚለዉ ግጥም በስንተኛዉ ስንኝ ላይ ይገኛል?

   ሀ/ 5 ለ/ 10

   ሐ/ 20 መ/ 9

ለ/ መምህሩ/ሯ ከመምህሩ መምሪያ ላይ አንበሳና ጦጣ በሚል የቀረበን ግጥም ሲያነቡላችሁ አዳምጡና በግጥም ሙያዊ ቃላት ላይ ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የግጥም ምንነትን ከዝርው ፅሁፍ ጋር ያለውን ልዩነት በተወሰነ ደረጃ ለማየት ችለናል፡፡ የነጠላና ውስብስብ ዓረፍተነገር ምንነት፣ከተሰጠው ፅሁፍ ወይም ዓረፍተነገሮች ደግሞ ነጠላና ውስብስብ በማለት ዓረፍተነገሮችን ለይተን አስቀምጠናል፡፡ የቃላት ተመሳሳይ ማለት በትረጉም የማይለወጡ ከተወከሉት ጋር አንድነት ያላቸው እንደሆነ ለማየት ችለናል፡፡ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን በፅሁፍ ውስጥ ለይተን ማስቀመጥ መቻላችንና መለማመዳችን ይታወሳል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ዘንድሮ የተዘራው እህል በጣም የለማ ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው

   ሀ/ የከሰመ ለ/ የቀጨጨ

   ሐ/ ፍሬ አልባ መ/ የዳበረ

2. ግጥም ከዝርው ፅሁፍ ከሚለይበት ነገር አንዱ

   ሀ/ ዘማዊ ነው ለ/ በአንቀፅ ይከፈላል

   ሐ/ ምት አለው መ/ ከ “ለ” በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው

3. የነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገርን ምንነት ከገለፃችሁ በኋላ ለእያንዳንዳቸው

   ምሳሌ ስጡ፡፡በሚከተሉት አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

   ሀ/ እና ለ/ ይሁን እንጂ

   ሐ/ስለዚህ መ/ ግን

5. ከግጥም ሙያዊ ቃላት ውስጥ ሁለቱን ተናገሩ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሶስት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ግጥም ምንነት መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የአረፍተ ነገር ምንነትና ዓይነትን መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በአረፍተ ነገር ውስጥ አያያዥ ቃላትን መጠቀም ችያለሁ፡፡ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ቴክኖሎጂ

### የምዕራፉ ዓላማዎች:-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ መልዕክቶችን አዳምጣችሁ ትገልፃላችሁ፡፡
- የቴክኖሎጂ አገልግሎትና ጠቀሜታን ትናገራላችሁ፡፡
- ከተለያዩ ጭዉዉቶችና ገለፃዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- የማስታወሻ አያያዝ መመሪያን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የአንቀፅን አፃፃፍ ስርዓትን ተከትላችሁ ተገቢ መሸጋገሪያ ቃላትን በመጠቀም አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር አንድ፡-

ሀ/ መምህሩ/ሯ በሚያዟችሁ መሰረት ለቀረበዉ ጥያቄ ምላሽ ስጡ፡፡

በዚህ ሳምንት ዉስጥ በብዙሃን መገናኛ የሚተላለፉትን ሀገራዊ የሆኑ መልዕክቶችን አዳምጣችሁ ወደ ክፍል በማምጣት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ተወያዩበት፡፡

1. መምህሩ/ሯ የሚያስደምጧችሁን ንግግር መነሻ በማድረግ ስላዳመጣችሁትነገር ማብራሪያ ስጡ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡-

ሀ/ ከታች የቀረቡትን ስዕሎች በማየት ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡













1. ከላይ የቀረቡትን ምስሎች በመመልከት የቴክኖሎጂ ዉጤቶች የሆኑና ያልሆኑትን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡
2. በለያችሁት የቴክኖሎጂ ዉጤት ጥቅሞች ላይ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ፡-**

1. ቴክኖሎጂ ባይኖር ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?
2. እናንተ አዘወትራችሁ የምትጠቀሙት የትኛዉን የቴክኖሎጂ ዉጤት ነዉ?

## የቴክኖሎጂ ጥቅምና ጉዳት

የቴክኖሎጂ ጥቅሞችና ጉዳቶች ማጣቀሻ የተደረገዉ ከቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አጠቃቀም ለሚመነጩ አዎንታዊና አሉታዊ መዘዞች ነዉ፡፡ ቴክኖሎጂ ለእነዚያ እድገታቸዉ ሳይንሳዊ እዉቀትን የሚጠይቁትን መሳሪያዎችን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

በዚህ ምክንያት ቴክኖሎጂ ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ላይ የተቆራኙትን የሰዎች ፍላጎት ለማርካት ያለመ የሳይንሳዊ እዉቀት ስብስብ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ እንዲሁም የዕለት ተዕለት ኑሮን ገፅታዎች ለማሻሻል ያስችላል፡፡

**የንባብ ጊዜ ጥያቄ**

ተማሪዎች እስቲ እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና በተከታዩ ጥያቄ ላይ ሀሳብ ተለዋወጡ፡፡

የቴክኖሎጂ ጥቅሞች የምንላቸዉ የትኞቹ ናቸዉ ? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ፡፡

ከቴክኖሎጂ ጥቅሞች መካከልም፡- መረጃንና እዉቀትን በቀላሉ ለማግኘት ይፈቅዳል፤ የግንኙነት መስመሮችን ያመቻቻል፤ በፍጥነት ለማቋቋም፤ ምርታማነትንና ቅልጥፍናን ይጨምራል፤ ለሰዎች ጤና አስተዋፅኦ ያደርጋል፤ አዳዲስ ሙያዎችን እና ስራዎችን ይፈጥራል፤ ጊዜ ቆጣቢ ነዉ፤ እኩልነትን ያራምዳል፤ ለሰዉ ልጅ ህልዉና ጠቃሚ ነዉ፤ የቤትና የዕለትተዕለት ተግባሮችን ቀላል ያደርጋል፤ ወዘተ. ናቸዉ፡፡ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች እያንዳንዱን ዘርዘር አድርገን ባናስቀምጥም ዉስኑን እንመለከታለን፡-

1. የመጓጓዣና የግንኙነት መስመሮችን ያመቻቻል፡- ከዚህ በፊት የሰዉ ልጅ ከአንድ አህጉር ወደ ሌላዉ ለመዘዋወር ጉዞዉን ከሶስት እስከ ስድስት ወር የሚወስድ መርከብ መውሰድ ነበረበት፡፡ በቴክኖሎጂ ግስጋሴዎች አሁን አዉሮፕላኖች በመፈጠራቸዉ አህጉሮችን በጥቂት ሰአታት ዉስጥ ማቋረጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም መኪናዎች ከመኖራቸዉ በፊት ሰዎች በፈረስ ላይ ይጓዙ ነበር፤ ግን አሁን በፍጥነትና በተራቀቁ ተሽከርካሪዎች ይሄዳሉ፡፡

2. የቤትና የዕለት ተዕለት ተግባሮችን ቀለል ያደርጋሉ፡፡ ዛሬ ለቴክኖሎጂ ምስጋና ይግባዉ ምግባችንን በተሻለ ሁኔታ ማቆየት ይቻላል፤ ምክንያቱም በማቀዝቀዣ (ፍሪጅ) ዉስጥ ማከማቸት ስለምንችል፤ ስለዚህ ከሌሎች በርካታ የዕለትተዕለት የህይወት ጉዳዮች ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡

እኩልነትን ያራምዳሉ፡- እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የአካል ጉዳተኛ ሆኖ የተወለደ ሰዉ እንደ ሌሎች ሰዎች ህይወት መኖር አይችልም ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- እንደ ዓይነ ስዉር ወይም መንቀሳቀስ የተሳነዉ ሰዉ ጉልበቱንና ዕውቀቱን በአግባቡ አይጠቀምበትም ነበር፡፡ ሆኖም ዛሬ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እኩልነትን ለማሳካት እድል የሚያጎለብቱ እንደ ቴሌ ስራን የመሳሰሉ ቴክኒኮችን አፍርተዋል፡፡

| |
|---|
| የቴከኖሎጂ ጉዳቱ ወይስ ጥቅሙ ያመዝናል? ተወያዩበት፡፡ |

## የቴክኖሎጂ ጉዳቶች፡

ስራ አጥነትን ሊጨምር ይችላል፡- ቴክኖሎጂ አዳዲስ ስራዎችን እንደሚፈጥር ሁሉ የድሮ ስራዎችን ያስወግዳል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ማሽኖችና ሮቦቶች በብዙ አካባቢዎች የሰዎችን ጉልበት በመተካት በተለይም ከትላልቅ እንዱስትሪዎች ጋር በተያያዙ የስራ መደቦች ላይ ስለሚተኩ፡፡

ለምሳሌ፡- ቀደም ሲል የሰዎች ቡድን የአንድ የተወሰነ ቁራጭ ፍሬዎችን የማጣበቅ ሃላፊነት ነበረዉ፡፡ ዛሬ ይህ እርምጃ በቀላሉ በማሽን ሊከናወን ተችሏል፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች ለጤና ጎጂ ነዉ፡- ቴክኖሎጂ በጤናዉ መስክ አስደናቂ ግስጋሴዎችን ለማዳበር ያስቻለዉ ቢሆንም ከመጠን በላይ በሆነ መንገድ በሚጠቀሙ ሰዎች ላይም ጉዳት ያስከትላል፡፡ ይህ ዓይናቸዉን የሚጎዱና ከዚያ በኋላ ዕይታ ላይ ችግር ሊያስከትሉ ከሚችሉ የሞባይል መሳሪያዎች ከመጠን በላይ የመጠቀም ሁኔታ ነዉ፡፡

**እዉነታን ያዛባል፡-** ቴክኖሎጂዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከተፈጥሮ የበለጠ እያራቁን እና በብዙ ገፅታዎች ከእዉነተኛ ህይወት እየወሰዱን ነዉ፡፡

ለምሳሌ፡- በይነመረቡ ወይም ምናባዊ እዉነታዉ በማያ ገፅ በኩል የሚከናወነዉን የነገሮች ግንዛቤ ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ለዉጥ አስከትሏል፡፡

ምንም አንኳን እንደ ማህበራዊ መገናኛ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ከቤት ሳይወጡ አለማትን እንድናውቅ ያደረገን ቢሆንም እዉነት ነዉ ይህ መረጃ ውድቀትን ወይም ሌላ አይነት አድሎአዊነትን እና ጭፍን ጥላቻን በመፍጠር በቀላሉ ሊዋዥቅ ይችላል፡፡

(ምንጭ፡- ኤስኤ( sf) 22 በትምህርት ዉስጥ የቴክኖሎጂ ጥቅሞችና ጉዳቶች እኤአ አፕሪል 2020 ከ future of working.com ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)፡፡

## ተግባር አንድ፡

### ሀ/ በምንባቡ መሰረት ለተከታዮቹ ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ ምረጥ/ጪ፡፡

1. ቴክኖሎጂ ከመምጣቱ በፊት የሰዉ ልጅ ለመጓጓዣነት ሲጠቀም የነበረዉ ነገር ፡-

   ሀ/ ፈረስ ለ/ አዉሮፕላን

   ሐ/ ዘመናዊ መኪና መ/ ሞተር

2. የቤትና የዕለትተዕለት ተግባራትን ቀላል የሚያደርጉት--------------ናቸዉ፡፡

   ሀ/ የሰዉ ልጆች ለ/ መኖሪያ ቤቶች

   ሐ/ ቴክኖሎጂ መ/ ትምህርት ቤት

3. በምንባቡ መሰረት ጉዳቱ "እዉነታን ያዛባል" የተባለዉ የቱ ነዉ?

   ሀ/ ብዕር/ እስክብርቶ/ ለ/ ቴክኖሎጂ

   ሐ/ ንፋስ መ/ መሬት

4. ከሚከተሉት መካከል አንዱ የቴክኖሎጂ ጥቅምን ይገልፃል፡፡

   ሀ/ መረጃን በቀላሉ ማግኘት ለ/ አካባቢን መበከል

   ሐ/ ሰዉን ማጋጨት መ/ መልስ የለዉም

5. እንደ ምንባቡ ሀሳብ ፍሪጅ ማለት፡-

   ሀ/ በረዶ ለ/ ዉብ

   ሐ/ ፈራጅ መ/ ማቀዝቀዣ (ምግብ ቶሎ እንዳይበላሽ የሚረዳ)

ለ/ በሳጥኑ ዉስጥ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸዉ፡፡ ከቃላቱ በመምረጥ ባዶ ቦታዉን አሟሉ፡፡

| | |
|---|---|
| አዎንታዊና አሉታዊ | ቴክኖሎጂ |
| አስተዋፅኦ | ማጣቀሻ |

1. የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አጠቃቀም --------እና --------መዘዞች አሉት፡፡
2. እዉነታን ከሚያዛቡ መካከል አንዱ---------------ሊሆን ይችላል፡፡
3. በአሁኑ ጊዜ ህይወትን ከሚያቀሉም ሆነ ከሚያወሳስቡ ነገሮች መካከል እንደ---------ቴክኖሎጂ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
4. ለሰዉ ጤና -------------ከሚያደርጉት ዉስጥ አንዱ ቴክኖሎጂ ነዉ፡፡

ሐ/ የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸዉ፡፡ ምንባቡ ዉስጥ ባላቸዉ አዉድ(ዙሪያ ገብ ንባብ) ፍቻቸዉን ግለፁ፡፡

ምሳሌ፡- መስክ- ዘርፍ

1. **ቁራጭ** _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
2. **ማዛባት**_ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
3. **ጎጂ** _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
4. **ህልዉና** _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
5. **ማስወገድ**_ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
6. **ተቆራኘ** _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
7. **ውስን** _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
8. **ጭፍን**_ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _
9. **ዋዝቀ** _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ማስታወሻ፡-

**አንቀፅ፡-** አንቀፅ ማለት አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለፅ ሲባል፣ በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሀሳብ ተዛምዷቸዉን የጠበቁ ዓረፍተ ነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርፅ ነዉ፡፡

**የአንቀፅ አፃፃፍ መመሪያ**

ሀ. አንቀፅ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ብቻ የሚያወራ መንደርደሪያ ዓረፍተነገር የያዘ አነስተኛ የፅሁፍ አካል መሆን አለበት፡፡

ለ. መንደርደሪያ ዓረፍተ-ነገር የአንቀፅ ፍሬ-ሀሳብ አጠቃሎ የያዘ መሆን አለበት፡፡

ሐ. መንደርደሪያ ዓረፍተነገር በአንቀፅ ዉስጥ የሚገኝበት ቦታ መገንዘብ መቻል ነዉ፡፡

መ. አንቀፁ ሲስፋፋ እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ከዋና ሀሳብ ወይምሀይለ ቃል ጋር ያለዉ ዉህደትና ቅደምተከተል የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

### ተግባር አንድ፡-

ሀ/ ከዚህ በታች የቀረቡት ዓረፍተነገሮች አያያዥ ቃላትን በተገቢዉ ቦታ በማስገባት ቅደም ተከተላቸዉን በማስተካከል አንድ አንቀፅ አድርጋችሁ ፃፉ፡፡ አንቀፁን ስትፅፉ የአንቀፅ አፃፃፍ መመሪያን ተከትላችሁ መሆን አለበት፡፡

1/ ተመልሼ ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን በላሁ፡፡

2/ ከእንቅልፌ ተነስቼ ልብሴን ለበስኩ፡፡

3/ ከስንደቅ ዓላማ መስቀል ስነ-ስርዓት በኋላ ወደ ክፍል ገባን፡፡

4/ ወደ ሽንት ቤት ሄድኩ፡፡

5/ ደብተሮቼን አሰናድቼ ወደ ተምህርት ቤት ሄድኩ፡፡

## ክፍል አምስት፡-ቃላት

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ምሳሌ፡-

| ቃል | ተመሳሳይ | ተቃራኒ |
|---|---|---|
| 1. ሰቆቃ | ዋይታ | ፍሳሃ |
| 2. ተሽማቀቀ | ፈራ | ተዝናና |
| 3. ቁንን | ጅንን | ልክስክስ |
| 1. ላመ | ------------------ | ------------------ |
| 2. ምሁር | ------------------ | ------------------ |
| 3. ስባት | ------------------ | ------------------ |
| 4. ቀልጣፋ | ------------------ | ------------------ |
| 5. መልካም | ------------------ | ------------------ |
| 6. ለገሰ | ------------------ | ------------------ |
| 7. ሁከት | ------------------ | ------------------ |
| 8. መጠየፍ | ------------------ | ------------------ |
| 9. ረሳ | ------------------ | ------------------ |
| 10. ቀላቀለ | ------------------ | ------------------ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስዉ

### ተግባር እንድ

ሀ/ በምሳሌዉ መሰረት ትክክለኛዉን ቃል በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ላይ ሙሉ፡፡

ምሳሌ፡- ሰዉነቴን -------------፡፡ /ወረረኝ፣ ቀደደኝ፣ ነዘረኝ/

1. ባለሀብቶች በተፈጥሮ አደጋ የተጎዱ አካባቢዎችን ለማቋቋም የእርዳታ እጃቸዉን -------፡፡ /ዘረጋችሁ፣ ዘረጉ፣ ዘረጋን/
2. ግለሰቦቹ የአጭበርባሪዎቹን አድራሻ-------------፡፡/ ጠቆሙ፣ ጠቆመች፣ ጠቆምኩ/
3. ለማስተማሪያ የተዋሱትን መፅሀፍ በጊዜ----------፡፡/ መለሰ፣ መለሱ፣ መለሰች/
4. ስንዱ ጓደኛዋ በርትታ እንድታጠና--------------፡፡/ መከረችሁ፣መከረቻት፣ ሳቀችባት/
5. ለስራችን ተስማሚ የሆነ ቦታ --------------------፡፡/ ተበታተንን፣ አገኘን፣ በላን/

6. ጌትነት ለተማረበት ትምህርት ቤት ገንዘብ-----------፡፡/ ለገሰ፣ ተማርኩ፣ እዉቀት/
7. ለአካለ መጠን ---------------፡፡/ አለፈ፣ ደረሰ፣ ሆነ/
8. በሽታ-------------------------፡፡/አንቆታል፣ ተቀብቶታል፣ ይዞታል/
9. ልብስ---------------------------፡፡ /አስጋገረ፣ አስቀደደ፣ አካሄደ/
10 /ፊት-----------------------------፡፡ / ፊካ፣ ጠወለገ፣ ነሳ/

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

### የማታወሻ አወሳሰድ መመሪያ

ማስታወሻ የሚያዝባቸዉ ጊዜያቶች፡-

- አንድን ነገር በምታደምጡበት ጊዜ
- ጉብኝት በምታደርጉበት ጊዜ
- በግል በምታነቡበት ጊዜ ወዘተ. ይሆናል፡፡

ማስታወሻ ስትይዙ የሚከተሉትን ነጥቦች አስተዉሉ፡-

1. ማስታወሻ መያዣ ወረቀትና ብዕር ወይም እርሳስ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡
2. ዋና ዋና ሀሳቦችን በቃላት፣ በሐረጋትና በዓረፍተ ነገር መፃፍ፡፡
3. ሁሉን ነገር ሳይሆን ዋና ዋና መረጃዎች ናቸዉ የምትሏቸዉን ብቻ መፃፍ፡፡
4. ማስታወሻ በዘገባ መልክ ሲዘጋጅ ግልፅ በሆነ ቋንቋና ቅደምተከተል ባለዉ መንገድ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

## ተግባር አንድ

1. የማስታወሻ አወሳሰድ መመሪያን በመከተል ጋዜጦችንና መፅሔቶችን በማንበብ ወይም ሬዲዮና ቴሌቪዥን በማዳመጥ ማስታወሻ ይዛችሁ፤ የአምስት ደቂቃ ማብራሪያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ስልትን በመጠቀም ስለ ቴክኖሎጂ ጥቅምና ጉዳት በሚገባ ተገንዝበናል፡፡ ቴክኖሎጂ እንደሚጠቅመን ሁሉ ጉዳትም ስላለው እንዴት መጠቀም እንዳለብንም እውቀት ገብይተናል፡፡ የማስታወሻ አያያዝ መመሪያን አውቀናል፤ በዚህ መሰረት ከተለያዩ ከምናዳምጠውም ሆነ ከምናነበው ማስታወሻ እንዴት መያዝ እንዳለብን ግንዛቤ ወስደናል፡፡ ቃላት በአውድ ውስጥ የሚሰጡንን ፍቺ ተረድተናል፡፡ እንዲሁም የአንቀፅ አፃፃፍ መመሪያን በመከተል አንቀፅን የመፃፍ ልምድንም አዳብረናል፡፡ በመጨረሻም ከየክፍላቱ ስር ያሉትን ተግባራት በማከናወን እውቀትን አግኝተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቴክኖሎጂ በጥቅሉ ፋይዳ ቢስ ነው፡፡ የተሰመረበት ሀረግ ፍቺ

   ሀ/ ጠቃሚ  ለ/ ጉዳት የለሽ  ሐ/ ጥቅም የለሽ  መ/ አሳሳቢ

2. የመንደርደሪያ ሀሳብ ሌላ ስሙ-----------------------ነው፡፡

   ሀ/ ሀይለ-ቃል ወይም ዋና ሀሳብ  ለ/ አንቀፅ
   ሐ/ ዝርው  መ/ ንኡስ ዓረፍተ ነገር

3. ከቴክኖሎጂ ጥቅሞች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
4. የማስታወሻ መመሪያዎች ከምንላቸው መካከል የተወሰኑትን ዘርዝሩ፡፡
5. ዘመዶቼ ዛሬ ወደ አዲስ አበባ-----------------( ገባን፣ ገባሁ፣ ገቡ)
6. ሁሉም ትምህርት ቤቶች በመስከረም ሁለት---------(ተከፈተች፣ይከፈታሉ፣ ተከፈታችሁ)

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል። በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ።

| | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ቴክኖሎጂ የቀረበውን ምንባብ ይዘት መግለፅ እችላለሁ። | | | |
| 2 | የአንቀፅ አፃፃፍ መመሪያን ዘርዘር እችላለሁ። | | | |
| 3 | የማስታወሻ አወሳሰድ ዘዴን ተረድቻለሁ። | | | |
| 4 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት ችያለሁ። | | | |
| 5 | ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት ችያለሁ። | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X ) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ አምስት

# ግብር ለሀገር ዕድገት

## የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ስለ ክርክር አድምጣችሁ ያዳመጣችሁትን ትናገራላችሁ፡፡
- ስለ ግብር አሰባሰብ በመጠየቅ የተገነዘባችሁትን በቃል ታስረዳላችሁ፡፡
- የምንባቡን ዓላማ ትረዳላችሁ፡፡
- ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ለምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ:-ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ያነበቡላችሁን ክርክር በማዳመጥ የክርከሩን ፍሬ ሀሳብ በራሳችሁ አባባል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሁለት :-መናገር

ማስታወሻ፡- ክርክር በሁለት የተለያዩ ቡድኖች መካከል የሚደረግ ስርዓት ያለው ሙግት ነው፡፡ በተቃራኒ ቡድኖች መካከል ይደረጋል፡፡ በክርክር ወቅት የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጉዳዮች ተከራካሪ ቡድኖች (ግለሰቦች) ዳኛ (ዳኞች)እና ታዛቢዎች መኖር አለባቸው፡፡

በክርክር ጊዜ ሊከናወኑ የሚገባቸው ነጥቦች፡-

- ማስታወሻ መያዝ
- አለባበስን አስተካክሎ መቅረብ
- በትህትና መናገር
- የክርክሩን ርዕስ ጠብቆ መናገር
- ክርክሩን መግቢያ፣ዝርዝርና መቋጫ ያለው ማድረግ
- የአድማጭን ችሎታ መገመት
- ሰዓት ማክበር
- የተቃራኒ ቡድንን ሀሳብ በደንብ ማዳመጥና መረዳት
- የዳኞችን ውሳኔ ማክበር

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በቡድን በቡድን ሆናችሁ ክርክር አካሂዱ፡፡ክርክር ስታካሂዱ የመከራከሪያ መመሪያን የተከተለ ይሁን፡፡

ለ/ በግብር አሰባሰብ ሂደት ዙሪያ ከወላጆቻችሁ፣ከአካባቢያችሁና ከባለሙያ በመጠየቅ የተገነዘባችሁትን ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

## ክፍል ሦስት፡-ማንበብ

### ቅድመ ንባብ

1. ግብርን የሚገብረዉ ወይም የሚከፍለዉ ማን ነዉ?
2. የግብርን ጥቅም ተናገሩ፡፡
3. ግብር ለሀገር ይጠቅማል? እንዴት?

## ግብር ማለት ምን ማለት ነው?

ግብር የመዝገበ ቃላት ፍችው ሲታይ መንግስት በህግና ደንብ ላይ ተመስርቶ ከህዝብና ከድርጅቶች ገንዘብ የሚያገኝበት መሳሪያ ነው፡፡ ዜጎች በመነገድ፣ቤትና ንብረት በማከራየት፣ዕውቀታቸውን በመሸጥ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ከሚያገኙት ገቢ ላይ በህግ በተቀመጠው መሰረት ግብር መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ስለዚህ ግብር ህብረተሰቡ ወይም ግብር ከፋዮች ለመንግስት በግዴታ ክፍያ የሚፈጽሙበት መንገድ ወይም ስርአት ሲሆን በአንጻሩ ግን መንግስት ለሕብረተሰቡ በለውጡ ወይም በምትኩ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ልዩነት ሳይፈጥር ለሚያቀርበው አገልግሎትና መሰረተ ልማቶች የሚያውለው ገንዘብ ነው፡፡

የግብር ወይም ታክስ አስፈላጊነትና ጥቅም

ግብር ከእያንዳንዱ ግለሰብ የየእለት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሲሆን ጠቀሜታዎቹም አያሌና ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ግብር ለኢኮኖሚ ልማት፣ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ለባህል እድገት፣ ለሀገር ደህንነት፣ ለፍትህና መልካም አስተዳደር መስፈን፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ሀገርን ከጠላት ለመከላከል፣የዘጎችን ደንነትና ሰላማቸውን ለመጠበቅ፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ መንገዶች፣የሀይል አቅርቦቶችን ለማስፋፋት ፣ኢኮኖሚን ለማነቃቃት፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ ልማትን ለማፋጠን፣የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፣ ኢኮኖሚን ለማረጋጋት፣ በዜጎች መካከል ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ለማድረግ እና የመሳሰሉት ስራዎችን ለማከናወን የሚውልና ከዘጎች የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው፡፡

## የግብር መርሆች፡--

አንድ የግብር ስርአት ሊከተላቸው ከሚገባ ዋና ዋና መርሆች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

ፍትሃዊነትን ወይም እኩልነትንና ገለልተኝነት መጠበቅ፡- የአገሪቱ የታክስ ስርዓት ሰዎች በሚያገኙት ገቢ ወይም በያዙት ሀብት አቅም በጎንዮሽና በሽቅቦሽ እኩል ግብር መክፈል እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው። ይህም ማለት ሰዎች ከሚያገኙት ገቢ ተመጣጣኝ የሆነ ግብር ልዩነት ሳይፈጥር ያለ አድሎአዊነት እንደየዘርፉ መክፈል እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው።

የታክስ ስርአቱ አስተዳደራዊ ወጪ ቆጣቢ መሆን፡- የታክስ ማስከፈያ ምጣኔው እና የታክስ ማዕቀፎቹ ይዘት ለመገንዘብና ለማስተዳደር ግለጽና ቀላል እንዲሆኑ በማድረግ የታክስ አከፋፈሉና ግዜው አመቺና በከፋዩ ላይ ውጣ ውረድ የማያስከትል እንዲሆን በማስቻል የታክስ አወሳሰኑና አሰባሰቡ የሚያስከትለው አስተዳደራዊ ወጪ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው።

ምርታማነት ወይም ውጤታማነት፡- የታክስ ስርዐቱ የመንግስትን የወጪ ፍላጎት ለመሸፈን በቂ ገቢ ማስገኘት እንደሚገባውና በሂደት ከራስ በሚሰበሰበው ገቢ የመንግሰትን አገልግሎቶችና መሰረተ ልማቶች ለማቅረብ የሚያስችለው መሆኑ ነው።

እርግጠኛና ምቹ መሆን፡- የአገሪቱ የታክስ ስርአት የግብር ከፋዩ አጠቃላይ ገቢ፣ ግብር የሚከፈለበት ገቢ እንዲሁም ከግብር ከፋዩ የሚፈለግ የግብርና የታክስ መጠን ላይ ለመድረስ የሚሰላበት አሰራር ወጥና በሁሉም ዘንድ በትክክል የሚታወቅ እንዲሆን ማድረግን የሚያመለክት ነው።

(http://www.mor.gov.et/ የገቢዎች ሚንስቴር ደህረ-ገፅ።)

## ተግባር አንድ

ሀ/ ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዓረፍተ-ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን እውነት ስህተት የሆኑትን ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ግብር ከእያንዳንዱ ግለሰብ የየእለት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡
2. ግብርን በወቅቱ መክፈል ለመሰረታዊ ልማት አስተዋፅኦ አለዉ፡፡
3. አንድ የግብር ስርዓት ከሚከተላቸው ዋናዋና መርሆዎች አንዱ የታክስ ስርዓቱ አስተዳደራዊ ወጪ ቆጣቢ አለመሆኑ ነው፡፡
4. ግብር ለሀገራዊ እድገት ፋይዳ የለውም፡፡
5. ግብር መክፈል የዜግነት መብት እንጂ ግዴታ አይደለም፡፡
6. አንድ ሀገር ፍትሃዊ የሆነ የግብር አሰባሰብ ስርዓት አለው፡፡

ለ/ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ደህንነት- ሰላም

1. የተቆራኘ
2. አያሌ
3. ፍትሃዊ
4. አድሎአዊነት
5. ምቹ

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ደብዳቤ፡-

አንድ ግለሰብ ለሌላ ግለሰብ፣ግለሰብ ለመስሪያ ቤት፣ መስሪያ ቤት ለሌላ መስሪያ ቤት የሚፅፈው መረጃ ለማስተላለፍ የሚጠቅም የስነፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

### የደብዳቤ ክፍሎች፡-

አንድ ደብዳቤ ሲፃፍ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ ናቸው፡፡

ሀ. መግቢያ፡- በዚህ የደብዳቤ ክፍል ቀን፣ወር፣ዓመተ ምህረት እንዲሁም ሰላምታ ይፃፍበታል፡፡ ደብዳቤው የመስሪያቤት ከሆነ ቁጥር፣ቀን፣ወር፣ዓመተ ምህረት የሚፃፍለት መስሪያ ቤት አድራሻና የጉዳዩ ርዕስ ይካተትበታል፡፡

ለ. ሐተታ፡- በዚህ ክፍል ሊተላለፍ የሚፈለገው መልዕክት በዝርዝር ይቀርብበታል፡፡

ሐ. መደምደሚያ፡- ከላይ በሐተታ ክፍል የቀረበው ዝርዝር ሀሳብ የሚጠቃለልበት ክፍል ነው፡፡ ደብዳቤው የግል ከሆነ የመሰናበቻ ሀሳብ፣የፀሐፊው ስምና ፊርማ ይቀርብበታል፡፡ ደብዳቤው የስራ ከሆነ ደግሞ የባለስልጣኑ ፊርማ፣የግርጌ ማህተም፣ግልባጭ የሚያስፈልገው ከሆነ ግልባጭ የሚፃፍላቸው መስሪያ ቤቶች ስም ይፃፋሉ፡፡

የጥሩ ደብዳቤ ባህሪያት፡

ሀ/ መልዕክቱ ግልፅና የማያሻማ መሆን አለበት፡፡

ለ/ መደበኛ ቃላት መጠቀም አለበት፡፡

ሐ/ በቂና የተሟላ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

መ/ ከስድብና ከመጥፎ ቃላት የራቀ መሆን አለበት፡፡

ሠ/ ትህትናና አክብሮትን በሚገልፅ ቃላት መደራጀት አለበት፡፡

ረ/ የተቀባዩን ስምና አድራሻ በግልፅ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

ሰ/ የደብዳቤ ህግና ስርዓትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

ሸ/ የተፃፈበትን ቀን፣ወርና ዓመተ ምህረት ማሳየት አለበት፡፡

## የደብዳቤ ዓይነቶች፡-

- ሁለት ዓይነት የደብዳቤ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም፡-
  ሀ/ የግል ወይም የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ እና
  ለ/ የስራ ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ናቸው፡፡
- ከቀረቡት የደብዳቤ አይነቶች በዚህ ክፍል የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ ብቻ የምናይ ይሆናል፡፡

  ሀ/ የግል ወይም የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ፡-

  ይህ ደብዳቤ አንድ ግለሰብ ለሌላ ግለሰብ ወይም ለመስሪያ ቤት የሚፅፈው የደብዳቤ ዓይነት ነው፡፡ ግለሰብ ለግለሰብ በተለያዩ ምክንያቶች ደብዳቤ ይፃፃፋሉ፡፡ ከነዚህ መካከል የፍቅር ደብዳቤ፣የምስጋና፣የይቅርታ፣የወቀሳ፣የሃዘን መግለጫ፣የማበረታቻ፣የግብዣ ጥሪ፣ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለዘመድ ወዳጅ ደብዳቤ ሲፃፍ ውስጣዊ ቅርፁ የሚከተለውን ይሆናል፡፡

--------ቀን (1)

------------------የላኪ አድራሻ (2)

---------------የተቀባይ አድራሻ (3)

______________________________________________

የመግቢያ ሰላምታ (4)

______________________________________________

______________________________________________

ሐተታ (5)

------------------------------------------------------------------------------

መደምደሚያ (6)

---------------የመዝጊያ ፊርማ (7)

------------------------- ስም (8)

- ይህን ቅርፅ ተከትሎ ከዚህ በታች የተፃፈውን ደብዳቤ አስተውሉ፡-

ቀን፡ 26/03/2013ዓ.ም

ተማሪ ኃይሉ ቶላ

ጄ/ዋቆ ጉቱ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት

የፖ.ሳ.ቁ. 4232

ፊንፊኔ

ለአባቴ አቶ ቶላ ጉርሙ

በሱሉልታ ወረዳ ጫንጮ ከተማ

የፖ.ሳ.ቁ.321

ጫንጮ

ውድ አባቴ አቶ ቶላ ጉርሙ፣ውድ እናቴ ወ/ሮ አለሚቱ ረጋሳ፣ውድ እህቴ አልማዝ ረጋሳ እንደምን ከርማችኋል? እኔ ከናንተ ናፍቆት በስተቀር እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፡፡ባለፈው ወር በማሙሽ ተስፋዬ በኩል የላካችሁልኝ ስንቅና 200ብር( ሁለት መቶ ብር) ደርሶኛል፡፡ በጣም አመሰግናችኃለሁ፤ምንም እኔ ልጃችሁ ብሆንም ውለታችሁ በጣም እየከበደኝ ያስጨንቀኛል፤በተለይም የቀን ስራ እየሰራችሁ ከጎረቤት ልጆች እንዳላንስ የምትፈፅሙት ተግባር ሲታወሰኝ እንባ በዓይኔ እየሞላ ተቸግሬያለሁ፡፡ውድ ዘመዶቼ ውለታችሁን ለመመለስ ሌት ተቀን እያጠናሁና ጥሩ ውጤት እያስመዘገብኩ ነው፡፡ በአንደኛ ሴሚስተር ከአርባ ተማሪዎች አንደኛ ወጥቼ በክፍል ኃላፊዬ በጣም ተመስግኛለሁ፡፡ በሁለተኛ ሴሚስተርም ከዚህ ያላነሰ ውጤት ለማስመዝገብ ከፍተኛ ጥረት እያደረኩ ነው፡፡ከአንድ ወር በኋላ የማጠቃለያ ፈተና ስለሚሰጥ ተፈትኜ እመጣለሁ፤በተረፈ እግዚአብሔር በአይነ ስጋ እስከሚያገናኘን ደህና ሁኑልኝ፡፡

ልጃችሁ ኃይሉ ቶላ

- በፖስታ ላይ የተቀባይና የላኪ አድራሻ አፃፃፍ፡-

ደብዳቤ ተፅፎ ከተጠናቀቀ በኋላ በፖስታ ታሽጎ የተቀባይና የላኪው አድራሻ ከተፃፈበት በኋላ ወደ ተፈለገበት አድራሻ ይላካል፡፡

በፖስታው ላይ የተቀባይና የላኪ አድራሻ ተፅፎ እንደሚከተለው ነው፡፡

- በፖስታው ጀርባ ላይ የሁለቱም አድራሻ ተፅፎ ሲታይ

ከ ----------
----------
----------

ለ ----------
----------
----------

## ተግባር አንድ

ሀ/ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ስለ ደብዳቤ በተማራችሁት መሰረት ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

1. የደብዳቤ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. የደብዳቤ አካላትን በቅደም ተከተል ጻፉ፡፡
3. የደብዳቤ ዋና ዋና አካላት ናቸዉ የሚባሉት-------፣------እና--------ናቸዉ፡፡
4. አንድ የሰላምታ ወይም የወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ ቅርጽ በመመልከት ከጻፋችዉ በኋላ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አንብቡ፡፡ የምትጽፉት ደብዳቤ ከላይ የቀረበዉን ቅርጽ መከተልአለበት፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

ማስታወሻ፡-

**ተቃራኒ ፊቺ፡-** ተቃራኒ ማለት አፍራሽ ማለት ነው። አንድ ቃል ለሚወክለው ነገር ተቃዋሚ ወይም አፍራሽ የሆኑ ቃላትን በመፈለግ እያዛመዱ ማጥናት ጠቃሚ ነው።

- ቃላትን በሚገባ እንድናውቅ ይረዳናል።
- ስለመነሻው ቃል ትርጉም፣ አገባብና ውክልና ጥርት ያለ ግንዛቤ እንድንጨብጥ ከማስቻሉም ባሻገር ሀሳቦችን በአሉታዊ አማራጭ ለማስተላለፍ እንድንችልም ይረዳናል።

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ፃፉ።

ምሳሌ፡- ሰባ- ጎፈየ

ደማቅ- ፈዛዛ

ሀሩር- ቁር

1. ፍቅር
2. በሳል
3. ጀግና
4. ድል
5. አዝናኝ
6. ረገሙት
7. ከበረ
8. ቁልቁል
9. መግቻ
10. ባእድ

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

### የቃል ክፍሎች

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዉስጥ የቃል ክፍሎች በአምስት ይከፈላሉ፡፡
አነሱም ፡-ስም ፣ግስ፣ቅጽል ፣ተውሳከ ግስና መስተዋድድ ናቸው፡፡

1. ስም፡- መጠሪያ የሆነ ማንኛውም ቃል ስም ይባላል፡፡

   ምሳሌ፡-

   ህልም ፣ፈረስ፣መሃመድ

2. ግስ ፡- ድርጊትንና የመሆን ስሜትን የሚገልጹ ወይም አንድን ዓረፍተ ነገር የሚያስሩ ወይም የሚቋጩ ቃላት ሁሉ ግስ ይባላሉ፡፡
   ከዚህ በታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች የተሰመረባቸው ቃላት ግስ ናቸው፡፡
   ለምሳሌ ፡-
   - ❖ ቦንሳ ልጁን መታው፡፡
   - ❖ ልጁ ጎበዝ ነው ፡፡

3. ቅጽል ወይም የስም ገላጭ፡- የሚባለዉ የንግግር ክፍል በስም ላይ ተጨምሮ የስሙን ዓይነት፣መጠን ወዘተ…የሚገልጽ ነው፡፡

   ምሳሌ፡-
   - ✓ አረንጓዴ ልብስ የለበሱ ወጣቶች መጡ፡፡
   - ✓ ኢትዮጵያዊው ቀነኒሳ በቀለን በሩጫ የሚበልጠው የለም፡፡

4. ተወሳከ ግስ ወይም የማሰሪያ አንቀጽ (የግስ) ገላጭ፡-ግስን ለመግለጽ የሚገባ ቃል ወይም ሀረግ ተዉሳከ ግስ ወይም የማሰሪያ አንቀጽ ገላጭ ይባላል፡፡ ተውሳከ ግሶች የቦታ፣የጊዜ፣የምክንያት እና የሁኔታ ወዘተ…በመባል ይጠራሉ፡፡
   ምሳሌ ፡-
   - ❖ እንጀጉ ከፉኛ ወደቀ፡፡

5. መስተዋድድ፡- በስም ወይም ስምን መስለው በሚገቡ ቃላት ላይ እየተጫነ ገብቶ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የንግግርን ዝምድና የሚያሳይ ቃል መስተዋድድ ይባላል፡፡ መስተዋድድ ሰዋስዋዊ ትርጉም ያለው ቢሆንም፤እንደ ሌሎች የቃል ክፍሎች አይራባም፡፡
   ምሳሌ፡-
   - ❖ መጽሀፉን ለእናቱ ሰጠ፡፡
   - ❖ ፋጡማ ወደ ጅማ ሄደች፡፡

## ተግባር አንድ

ሀ/ ቀጥሎ የቀረቡትን መስተዋድዶች ከታች በቀረቡት ባዶ ቦታዎች ውስጥ በተገቢ ሁኔታ አስቀምጡ፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አስከ- | | ለ- | | ወደ- | | ስለ- |
| እንደ- | | ከ- | | በ- | | እየ- |

1. ----------ቤቱ ድረስ ሸኘውት፡፡
2. ---------ተራበ መስራት የለበትም፡፡
3. ሁሉም ህፃናት------------ትምህርት ቤት መሄድ አለባቸው፡፡
4. ሰውን-----------------ፍቅር መያዝ መልካም ነው፡፡
5. ---------------ሀረር የመጣው ትናንት ነው፡፡
6. -------------ጀግና መኮፈስ ይወዳል፡፡
7. ሔለን-----------ተቸገሩ ጎረቤቶቿ ደራሽ ናት፡፡
8. -----------መከርኳት ተነስታ ሄደች፡፡

ለ/ ከታች የቀረቡትን መስተዋድዶች ከግስና ከስም ጋር አጣምሩ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ለ- | | በ- | | ከ- |
| እስከ- | | ወደ- | | ስለ- |

ምሳሌ፡- ለአልማዝ መፅሐፍ ተገዛላት፡፡

- አዲሱን ቤት በመግዛቴ ተደሰትኩ፡፡

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

**ምሳሌያዊ ንግግር**

ማስታወሻ፡- የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግር በአማርኛ ተናጋሪው ህብረተሰብ ውስጥ ተፈላጊነትና ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ፡፡ ምሳሌያዊ ንግግር ቀደም ሲል የተነገረን አነጋገር ለማጠናከር የበለጠ ግልፅ ለማድረግና ለዛ ለመስጠት ሲፈለግ በንግግር ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚቀርብ አባባል ነዉ፡፡ በምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዎች ደስታቸዉን፣ ሀዘናቸዉን፣ እምነታቸዉን፣ ወዘተ. ይገልፁበታል፡፡

አስፈላጊና ጎጂ ባህሎችን ያወግዙባቸዋል፤ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑትን ያወድሱበታል ወዘተ.፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች ከቃላዊ ስነ-ፅሁፍ ዉስጥ ይመደባል፡፡

ምሳሌ፡- ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል፡፡

- ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ፡፡
- የፈሰሰ ዉሃ አይታፈስም፡፡
- አተርፍ ባይ አጉዳይ፡፡
- የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል፡፡
- ሳይቃጠል በቅጠል፡፡
- ታጥቦ ጭቃ፡፡

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከዚህ በታች ያሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሙሉ የሚያደርጉ ትክክለኛ ሀረጎችን ምረጡ፡፡

ምሳሌ፡- የፉክክር ቤት፣---------------------፡፡

መልሱ፡- ሳይዘጋ ያድራል

1. ህመሙን የሸሸገ፣-----------------------፡፡
   ሀ. መድሃኒት ይፈልጉለታል ሐ. ሳይታከም ሞተ
   ለ. መድሃኒት አይገኝለትም መ. ብዙ ተሰቃየ
2. ለተቀማጭ፣---------------------------------፡፡
   ሀ. ሰማይ ቅርቡ ነው ሐ. አትንገረው
   ለ. ወሬ አያመልጠውም መ. ጎበዝ ቆንጣጭ

3. ሞኝ ቢያከብሩት፣---------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. ያከብራል | ሐ. የፈሩት ይመስለዋል |
| ለ. ይኮራል | መ. ያሳፍራል |

4. ሰነፍ እረኛ፣---------------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. አይሆንም ዘበኛ | ሐ. አይሆንም አንደኛ |
| ለ. ከሩቅ ይመልሳል | መ. የከብት ቀበኛ |

5. ሰነፍ ገበሬ፣-----------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. ቆቡን ቀዶ ይሰፋል | ሐ. ጢስ ይሞቃል |
| ለ. በሰኔ ይሞታል | መ. አፍሶ ይለቅማል |

6. ቀጥኜ ቢያዩኝ፣----------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. ሰደቡኝ | ሐ. ጅማት ለመኑኝ |
| ለ. ተቆጡኝ | መ. አባረሩኝ |

7. በእጅ የያዙት ወርቅ፣-----------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. ሰውነት አያደምቅ | ሐ. ከመዳብ ይቆጠራል |
| ለ. ያንደላቅቃል | መ. ያኮራል |

8. አፍንጫን ቢመቱት፣------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. ያማል | ሐ. አይን ያለቅሳል |
| ለ. ያለቅሳል | መ. ያቃጥላል |

9. እኔ ከሞትኩ፣--------------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. ሰርዶ አይብቀል | ሐ. ምን ቸገረኝ |
| ለ. የትም ልቀበር | መ. ማንም ይሙት |

10.ወስፈጤ ሲለግም፣---------------------------::

| | |
|---|---|
| ሀ. አይሰፋም | ሐ. አይገደድም |
| ለ. ቅቤ አይወጋም | መ. ጠንካራ ይሆናል |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በመነሻውም ስለ ግብር

ምንነት፣ጠቀሜታና አስፈላጊነት በስፋት ተመልክተናል፡፡ ግብርን በተመለከተ የተለያዩ ተግባራትን ሰርታችዋል፡፡

በመቀጠል የክርክር መመሪያ ወይም ደንቦች የተመለከትን ሲሆን በስሩ የተለያዩ ተግባራትን ሰርታችዋል፡፡ ከዚያም ስለ ቃላት ፍቺ ባነሳንባቸው ክፍሎች የቃላት ትክክለኛው ተመመሳሳይና ተቃራኒ የሚለየው በገቡበት አውድ እንደሆነ አይተናል፡፡

በመቀጠል የደብዳቤ አይነቶች፣ክፍሎችና ባህሪያትን አንድ በአንድ የተመለከትን ሲሆን አምስቱን የቃል ክፍሎችንም በዝርዝር ተመልክተናል፡፡

በመጨረሻም የምሳሌያዊ አነጋገር ምንነትና ምሳሌዎችን በሚገባ አይተናል፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የግብር ምንነትንና ጥቅም ዘርዝሩ።
2. የክርክር መመሪያዎችን ግለፁ።
3. የደብዳቤ ክፍሎችና ባህሪያትን ዘርዝሩ።
4. የምሳሌያዊ አነጋገር ምንነትና ጥቅም ዘርዝሩ።

➢ ከታች ለቀረቡት ምሳሌያዊ ንግግሮች ፍቺ ስጡ።

ሀ/ ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፣ለሃምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው።

ለ/ ሀብት የጥዋት ጤዛ ነው።

ሐ/ ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት።

መ/ ሆድ ከሀገር ይሰፋል።

ሠ/ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ።

ረ/ ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም።

5. ትልቋ አያንቱ በትምህርት አንደኛ ወጣች። የተሰመረበት የቃል ክፍሉ--

   ሀ/ ስም   ለ/ ቅፅል   ሐ/ ተውሳከ ግስ   መ/ መስተዋድድ

6. መምህሩ ወደ ክፍል በፍጥነት ገቡ። የተሰመረበት የቃል ክፍሉ

   ሀ/ ተውሳከ ግስ ለ/ ቅፅል ሐ/ ግስ መ/ መስተዋድድ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ግብር አሰባሰብና ጥቅም ሂደትን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የክርክር ሂደትን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |
| 4 | የአያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት አገልግሎት ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ስኬት

## የምዕራፉ አበይት ዓላማዎች፡-

- ስኬትን የተመለከተ የመገናኛ ብዙሃን ፕሮግራሞችን ተከታትላችሁ ያዳመጣችሁትን ሐሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- የጭውውት መመሪያን ተከትላችሁ በሚሰጣችሁ ርዕስ ላይ ጭውውት ታካሂዳላችሁ፡፡
- ምንባቡን በለሆሳስ ታነባላችሁ፡፡
- ከቀረቡት ቃላት የሚጠብቁና የሚላሉ ድምፆችን ለይታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- የቃል፣ የሀረግና የዓረፍተነገር ልዩነትና አንድነትን ትለያላችሁ፡፡
- መመሪያን ተከትላችሁ ከሚቀርብላችሁ ፅሁፍ ገፀባህሪያትን ትለያላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

1. ቀጥሎ መምህራችሁ በየረድፉ መጀመሪያ ላይ ለተቀመጡ ተማሪዎች አንዳንድ ዓረፍተነገር በጆሮአቸው ይነግራሉ፡፡ መልዕክቱን ተቀብላችሁ አጠገባችሁ ላለ ተማሪ በሹክሹክታ ንገሩ፡፡ በዚህ ዓይነት እየተቀባበላችሁ በማሳለፍ የረድፋችሁ የመጨረሻው ተማሪ የደረሰውን መልዕክት ለመምህራችሁ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገር፤ መጀመሪያ ላይ ከተነገርው መልዕክት ጋር አነፃፅሩ፡፡

2. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ "ለተሻለ ውጤት በርትታችሁ አጥኑ" የሚል አንድ አጭር ታሪክ ሁለት ጊዜ ብቻ ያነቡላችኋል፤ በጥሞና አዳምጣችሁ ታርኩን እንደገና በራሳችሁ አባባል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ/ ቀጥሎ ያለውን ምሳሌ በመከተል በቡድን በቡድን ሆናችሁ የሚና ጨዋታ ተጫወቱ፡፡

ምሳሌ፡- በመምህርና ተማሪ መካከል የተደረገ የሚና ጨዋታ፡-

መምህር፡- የቤት ስራሽን ሰራሽ አያንቱ?

አያንቱ፡- አዎን መምህር፡፡

መምህር፡- አያንቱ እስቲ አምጪው!

አያንቱ፡- እሺው! ትናንት በነገሩኝ መሰረት ምንባቡን አንብቤ የተሰመረባቸውን ቃላት

ትረጉም ፅፌያለሁ፡፡

መምህር፡- ጥሩ ነው፡፡ ተማሪ የቤት ስራ ሲሰጠው ሰርቶ መምጣቱ የተማሪውን ትጉህ መሆን ያመለክታል፡፡ የቤት ስራን የማይሰራ ተማሪ በትምህርቱ ውጤታማ አይሆንም፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪውን ይጎዳል፤ የመምህሩንም ልፋት ከንቱ ያደርጋል፡፡

አያንቱ፡- ልክ ነው፡፡ እናቴም የምትመክረኝ "የመምህርሽን ትዕዛዝ ብታከብሪ ውጤታማ ትሆኛለሽ፡፡ ይህ ደግሞ የወደፊት ህይወትሽን የተቃና ያደርገዋል" ብላኛለች፡፡

መምህር፡- ጥሩ ብላሻለች፡፡ በርትቶ የሰራ ውጤታማ ይሆናል፡፡

3. ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት መከባበር የተሞላበት የሚና ጨዋታ ተጫወቱ፡፡

1.እናትና ልጅ በመሆን

2.ሐኪምና ታካሚ በመሆን

**ክፍል ሶስት፡- ማንበብ**

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ስኬት ምንድን ነው?
2. ስኬታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?
3. የስኬታማ ሰዎችን የህይወት ተሞክሮ መመልከት ወይም ማዳመጥ ምን ጥቅም አለው?

## የስኬት መንገዶች

"ስኬታማ የሆኑ ሰዎች ልምድ" በስቴቨን ኮቬይ ተደርሶ የቀረበው መፅሐፍ ገና ከመጀመሪያው "ውስጣዊ ድል ከውጫዊ ድል ይበልጣል" በማለት የሚጀምረው መፅሐፉ እዚህ ምድር ላይ ማግኘት የምንፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ለማግኘት አስቀድመን ራሳችንን ማሸነፍ፤ የህይወታችን ሾፌር መሆን፤ ውስጣዊ ማንነታችንን መቆጣጠር፣ወዘተ. አለብን ማለት ነው፡፡ "ከተማን ከሚመራ ሰው ይልቅ ራሱን የሚመራ ሰው ይበልጣል" ይላል ጠቢቡ ሰለሞን፡፡

ራስን ማሸነፍ ሌሎች ውጫዊ ነገሮችን የማሸነፊያ ቁልፍ ነው፡፡ በመቀጠል በቅደም ተከተል የምንመለከታቸው ሰባት የስኬት መንገዶች የማንኛውም ሰው የግል ህይወት መሪ እንዲሆን በእጅጉ የሚያግዙ ናቸው፡፡

1. ኃላፊነት ውሰዱ ጅብ ከሄደ በኋላ የውሻ መጮህ ምንም ውጤት አያመጣም፤ ትርፉ ድካም ነው፡፡ ውጤት የሚያመጣው ጅቡ ከመምጣቱ በፊት አስቀድሞ በማነፍነፍ ድምጽ ማሰማት ነው፡፡ ሁኔታዎችን፣ ሌሎች ሰዎችን፣ ዓለምን፣ ወዘተ. የሚወቅሱ ሰዎች በህይወታቸው የረባ ቁም ነገር አያከናውኑም፤ ሁልጊዜም ኃላፊነትን የሚያሸክሙት ከእነሱ ውጪ ላለ ሌላ አካል ነው፡፡ ኃላፊነትን መሸከም ስንችል ነው የህይወታችንን ጉዞ አቅጣጫ መወሰን የምንችለው፡፡ የተሽከርካሪውን መሪ ለሌላ አካል አሳልፈን ሰጥተን የምፈልገው ቦታ አይደለም የደረስኩት፤ በፈለኩት ፍጥነት አይደለም እየተጓዝኩ ያለሁት፤ ወዘተ. ልንል አንችልም፤ ብንልም ዋጋ የለውም፡፡

የጉዞውን አቅጣጫ፣ ፍጥነት እና አድራሻ የሚወስነው አሽከርካሪው ነው፡፡ ልምዳችን መውቀስ፣ ጣት መጠቆም፣ ራስን መከላከል፣ ወዘተ. ከሆነ እውነቱን ለመናገር የሚወቀስ ነገር ማግኘት አይከብድም፡፡ ዘወትር የእናቴ መቀነት አደናቅፎኝ ነው ማለት ህይወታችን ባለህበት እርገጥ እንዲሆን በር ወለል አድርጎ ይከፍታል፡፡ ስለዚህ ለውጥ ለማምጣት፣ የራሳችን ሰዎች ለመሆን፣ ውስጣችንን ድል ለማድረግ፣ ወዘተ. ሁልጊዜም ለገዛ ራሳችን ህይወት ሙሉ ኃላፊነት እንውሰድ፡፡ ቃላችንን የምናከብር፤ በአልንበት ቦታ የምንገኝ፤ በገዛ ራሳችን ጥረት የምንፈልገውን ማንኛውንም ዓይነት ነገር እጃችን ለማስገባት መጓዝ ያለብንን ያህል ርቀት መጓዝ የምንችል ሰዎች እንሁን፡፡

"ስራ እኮ ጠፋ! እኔ ምን ላድርግ?" ከማለታችን በፊት ስራ ለማግኘት የምንችለውን ድንጋይ በሙሉ መፈንቀላችንን እርግጠኛ እንሁን፤ ቀጣሪዎች የሚፈልጉትን ዕውቀት እና ክህሎት ይዘን ለመገኘት ጥረት እናድርግ፤ የተለመደውንም ያልተለመደውንም አማራጭ እንፈትሽ፡፡

2. የምትፈልጉትን ነገር አስቀድማችሁ እወቁ ስቴቨን ኮቪይ "ነገሮች ሁለት ጊዜ ይፈጠራሉ" ይላል፡፡ የመጀመሪያው ፈጠራ የሚጠናቀቀው አእምሮአችን ውስጥ ነው፡፡ ከቤት ከመውጣታችን በፊት የምንሄድበትን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ከአንድ እና ሁለት፣ አምስት እና አስር ዓመት፣ ወዘተ. በኋላ ምንድን ነው ማግኘት፣ ማድረግ፣ መሆን፣ ወዘተ. የምንፈልገው? ለእነዚህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ መስጠት ነገሮቹ በተጨባጭም ወደ ህይወታችን የሚመጡበትን ዕድል ከፍ ያደርጋል፡፡ የምናገኘው የምናስበውን ነው፤ የምንደርሰው እንደርሳለን ብለን የምናስበው ከፍታ ድረስ ነው፡፡

ግባችንን ማወቃችን ትኩረታችንን ለመሰብሰብ ይረዳናል፤ ከነፈሰው ጋር አንነፍስም፤ በፈተና መካከል ፀንተን እንቆማለን፡፡

3. ቅድሚያ ለሚገባቸው ነገሮች ቅድሚያ ስጡ "ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት" ይባላል፡፡ ቅድሚያ መስጠት ላለብን ነገሮች ቅድሚያ መስጠት አለብን፡፡ ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ ላይ አይወጣም፡፡ ኮቬይ እንዲህ ይላል፡- "ራሳችሁን ከእነዚህ ሶስት አጉል  ልምዶች በአንዱ መውቀስ ቢኖርባችሁ በየትኛው ነው የምትወቅሱት? (1) መስራት ያለብኝን ነገር በቅደም ተከተል መለየት አልችልም፤ (2) በአስቀመጥኩት ቅደም ተከተል መሰረት መስራት አልችልም፤ (3) በወሰንኩት ቅደም ተከተል መሰረት ለመስራት አስፈላጊው ቁርጠኝነት የለኝም፡፡ ብዙ ሰዎች ቁርጠኝነቱ የለኝም ነው የሚሉት፡፡ ጠለቅ ብለን ከመረመርነው ግን እውነቱ ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እውነቱ ቅደም ተከተሉ ውስጣችን በጥልቀት አለመስረጹ ነው፡፡ የህይወት ግባችንን አስቀድመን በሚገባ ለይተን በሚገባ ውስጣችንን መቅረጽ አለመቻላችን ነው"፡፡

4. በጋራ እኩል ተጠቃሚነት መርህ ተመሩ ከተቃራኒ ፆታ ጀምሮ እስከ የንግድ ስራ ግንኙነት ድረስ በጋራ እኩል ተጠቃሚነት መርህ መመራት ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ በእኩል ተጠቃሚነት መርህ ነው ህይወቴን የምመራው፡፡" ትሉ ይሆናል፡፡ እንደምትሉት እንደምትኖሩ ግን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ ለማሸነፍ ከመጣር ይልቅ በጋራ እኩል ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት አድርጉ፡፡ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን፣ ከሌላው ከፍ ብሎ ለመታየት፣ ልክ ሆኖ ለመገኘት፣ወዘተ. ከመጨነቅ ይልቅ በጋራ እኩል እንዴት ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ማሰብ እና ይህንን መርህ በየትኛውም የግንኙነታችን መረብ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገናል፡፡

5. መጀመሪያ ለመረዳት ጥረት አድርጉ መጀመሪያ ስንረዳ የሚረዱንን እናገኛለን፡፡ ብዙ ጊዜ ግን በአንጻሩ ጊዜያችንን የምናጠፋው ሰዎች እንዲረዱን በመፍጨርጨር ነው፡፡ ቆም ብለን "ምንድነው እስኪ እያሉ ያሉት? ልክ ይሆኑ ይሆን? በየትኛው ማዕዘን ነው እነሱ ጉዳዩን ያዩት?" ወዘተ. ብሎ በቀናነት ማሰብ እና ሰዎችን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ጥሩ ነው፡፡ ሰዎችን የመረዳት ችሎታችን ጥሩ ሲሆን የሚረዱንን ሰዎች ቁጥርም ይጨምራል፡፡

6. “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” ትልቅ መልዕክት ያለው አባባል ነው፡፡ በጋራ የሚሰሩ ስራዎች በግል ከሚሰሩ ስራዎች ይልቅ የላቀ ውጤት ያመጣሉ፡፡ አንድ እጅ ብቻውን አያጨበጭብም፡፡ ሩጫን በመሰለ የግል ጥረትን በከፍተኛ ሁኔታ በሚጠይቅ የውድድር ዘርፍ እንኳን አትሌቶቻችን ሲተባበሩ የሚያስመዘግቡትን አንጸባራቂ ድል

እናውቀዋለን፡፡ በየትኛውም አጋጣሚ በጋራ የመስራትን መንፈስ ማዳበር ጠንካራ ያደርጋል፤ የበዛ ፍሬም ያፈራል፡፡ አብረን መብላት ብቻ ሳይሆን አብረን መስራትንም ባህላችን እናድርግ፡፡ ስቴቨን ኮቬይ እንደሚለው “አንድ ሲደመር አንድ ከሁለት በላይ ነው”፡፡

7.“መጋዛችሁን ሳሉ” የሚል በስቴቨን ኮቬይ መጽሐፍ ውስጥ ግሩም አፈ ታሪክ አለ፡፡ አንድ ተጓዥ መንገደኛ በአንድ ጫካ ውስጥ አቋርጦ ሲያልፍ አንድ ምስኪን እንጨት ቆራጭ ላቡ ጠፍ እስከሚል ድረስ ያለምንም እረፍት እንጨት ሲቆርጥ ይመለከታል፡ ፡ ተጓዡ መንገደኛ ቆም ይልና የመጋዙን መደነዝ አስተውሎ ኑሮ “ወዳጄ! ለምን መጋዝህን ዕረፍት ወስድህ አትስለውም?” ይለዋል፡፡ ልፋ ያለው እንጨት ቆራጭ “አይ ለሱ እንኳን ጊዜ የለኝም” የሚል የዋህ ምላሽ ይሰጠዋል፡፡ ይኼ ምስኪን እንጨት ቆራጭ ዕረፍት ወስዶ መጋዙን ቢስል በተሻለ ቅልጥፍና ብዙ እንጨት መቁረጥ እንደሚችል አልተረዳም፡፡ የተራ ቁጥር ሰባት ልምድ መልዕክት ቀላል
እና ግልጽ ነው፡፡ በቂ ዕረፍት ምንጊዜም አድርጉ ነው፡፡
ከስራ በኋላ ራሳችሁን ዘና የማድረግ ልምምዱ ይኑራችሁ፡፡ መዝናናት ለጊዜው ከሚሰጠው ደስታ ባሻገር ለቀጣይ ስራ ያዘጋጃል፡፡ ትልልቅ ኩባንያዎች ወጪ ችለው፣ ወርሃዊ ደሞዝ መክፈላቸውን ሳያቋርጡ ሰራተኞቻቸውን የሚያዝናኑት በጣም ቸር ስለሆኑ አይደለም፡፡ ይልቁንም የተዝናና ሰራተኛ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን እና እነሱንም ይበልጥ ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች “እኔ መዝናናት አይሆንልኝም” ይላሉ፡፡

“መዝናናት ራሱን የቻለ ችሎታ ነው” የሚሉም አሉ፡፡ በመሆኑም “እንዴት እንዝናና?” የሚል ጥያቄ ያላችሁ ሰዎች እነዚህን የመዝናኛ አማራጮች እንድትፈትናቸው እጋብዛለሁ፡- ዋና ዋኙ፤ ከወዳጅ ዘመዶቻችሁ ጋር አስደሳች ጊዜ አሳልፉ፤ ከከተማ ከተቻለም ከሀገርም ወጣ ብላችሁ ጎብኙ፤ ደስታ ይሰጠኛል ብላችሁ የምታስቡትን የትርፍ ጊዜ የመዝናኛ አማራጮችን እንደየ አካባቢያችሁ ነባራዊ ሁኔታ መሞከር፣መፈተሽ ጠቃሚ ነው፡፡

(ምንጭ፡- www.yerasbusiness.com)

## ተግባር አንድ

ሀ/ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚ መልስ ምረጡ።

1. ሌሎች ውጫዊ ነገሮችን የምናሸንፍበት ቁልፍ ነገር---------------ነው።
   ሀ/ ከራስ ጋር መጣላት
   ለ/ ራስን ማሸነፍ
   ሐ/ ከሰው ጋር አለመስማማት
   መ/ መሮጥ
2. በአብዛኛው ኃላፊነትን መውሰድ የማይፈልጉ ሰዎች በህይወታቸው----አያከናውኑም።
   ሀ/ የረባ ቁምነገር ለ/ ፍቅርን
   ሐ/ ጥላቻን መ/ ሰውን
3. ኃላፊነትን መሸከም ስንችል፡-
   ሀ/ የህይወታችንን ጉዞ አቅጣጫ መወሰን አንችልም
   ለ/ የሰው የህይወት ጉዞ አቅጣጫ ውስጥ ጣልቃ እንገባለን
   ሐ/ የህይወት ጉዞ አቅጣጫ መወሰን እንችላለን
   መ/ ሁሉም መልስ ይሆናል
4. ምንባቡ "የእናቴ መቀነት አደናቅፎኝ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   ሀ/ ጥሩ ስራን መስራት ለ/ ዘዴን መዘየድ
   ሐ/ ተስማምቶ መስራት መ/ ለስራ ሰበብ መፈለግ
5. እንደ ምንባቡ አገላለፅ ፈጠራ የሚጠናቀቀው --------ውስጥ ነው።
   ሀ/ አዕምሮአችን ውስጥ ነው ለ/ ስንፅፍ ነው
   ሐ/ ስናነብ ነው መ/ ስራ ላይ ስንሆን ነው

ለ/ በምድብ "ሀ" ስር ለሚገኙት ቃላት ተቃራኒ ይሆናሉ የተባሉ ቃላት በምድብ "ለ" ስር ተዘርዝረዋል። ይበልጥ የሚስማማውን እየመረጣችሁ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መሪ | ሀ. ውጫዊ |
| 2. ዘወትር | ለ. ውድቀት |
| 3. የረባ | ሐ. ተከታይ |
| 4. ውስጣዊ | መ. እርባና ቢስ |
| 5. ስኬት | ሠ. አልፎ አልፎ |

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ተግባር አንድ

1. በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ስለሚወራ ስለ ታዋቂ ሰዎች ወይም ስለ ታዋቂ አርበኞች ሰዎችን ጠይቃችሁ ያገኛችሁት መረጃ በፅሁፍ አጠናክራችሁ አቅርቡ፡፡
2. የስደትን አስከፊነት የሚገልፁ ሀሳቦች ከተለያዩ ግለሰቦች በመጠየቅ ከአምስት ዓረፍተ-ነገር ባልበለጠ ፅሁፍ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡
3. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ቃላት ወይም ሀረጋት በጥሞና አድምጣችሁ የተነበበላችሁን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት

በቃል ውስጥ በሚገኙ ድምፆች መጥበቅና መላላት የትርጉም ልዩነት ሊፈጠር ይችላል፡፡ በአማርኛ ጠባቂ ድምፆች የሚገኙበት ቦታ በቃል መሃከልና መጨረሻ ላይ ነው፡፡ በቃል መጀመሪያ ያለ ድምፅ አይጠብቅም፡፡

ለምሳሌ፡- በድምፅ መላላትና መጥበቅ ምክንያት የተፈጠሩትን የፍቺ ልዩነቶችን እንመልከት፡-

| | ቃል | ሲላላ ፍቺው | ሲጠብቅ ፍቺው |
|---|---|---|---|
| 1. | ለጋ | ያልበሰለ | መታ |
| 2. | ልረዳ | ላግዝ | ላውቅ፣ልገነዘብ |
| 3. | መና | ከንቱ | ከባዶ የተገኘ |
| 4. | ሰፊ | ልብስ በመርፌ የሚሰፋ | ጠባብ ያልሆነ |
| 5. | ሽፍታ | አመፀኛ | በሰውነት ላይ የሚወጣ ነጠብጣብ |

## ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች የቀረቡትን ቃላት በድምፅ መላላትና መጥበቅ ምክንያት የተፈጠሩ የፍቺ ልዩነቶችን አሳዩ፡፡

| ምሳሌ፡- | ቃል | ሲላላ | ሲጠብቅ |
|---|---|---|---|
| 1. | አያት | የአባትና የእናት ወላጆች | ተመለከታት |
| 2. | ይመጣል | ከሄደበት ይመለሳል | ይስባል |
| 3. | ገና | --------------- | ------------- |
| 4. | በራ | --------------- | ------------- |
| 5. | በላ | --------------- | ------------- |
| 6. | ስንቅ | --------------- | ------------- |
| 7. | ቀና | --------------- | ------------- |
| 8. | ዓባይ | --------------- | ------------- |
| 9. | አዛባ | --------------- | ------------- |
| 10. | ዋና | --------------- | ------------- |
| 11. | ጠላት | --------------- | ------------- |
| 12. | ፍራሽ | --------------- | ------------- |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋሰው

### የቃል፣ የሀረግና የዓረፍተ-ነገር ልዩነቶች

**ቃል**፡- በድምፆች ቅንብር የሚፈጠር ትርጉም ያለው የንግግር ክፍል ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሄደ ጠረጴዛ መሰላል

**ሀረግ**፡- ከቃላት ቅንብር የሚፈጠር የተሟላ ስሜትን የማይሰጥ የንግግር ክፍል ነው፡፡

ምሳሌ፡- የአቶ ለሜሳ ላም

በመኪና መንገድ

ዓረፍተነገር፡-ስሜትን የሚሰጥ የቃላት ወይም ሀረጎች ስብስብ ነው።

ምሳሌ፡- ልጁ መጣ።

ቀይ ሸሚዝ ገዛሁ።

ኩምሳ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ።

## ተግባር አንድ

ሀ/ ከዚህ በታች ከቀረቡት ውስጥ ቃል ከሆነ "ሀ" ሀረግ ከሆነ "ለ" ዓረፍተነገር ከሆነ "ሐ" በማለት መልስ ስጡ።

1. ፀሐይ ወጣች -----------------------------------
2. ወሳኝ -------------------------------------------
3. ልጂቱ በወርቅ አጌጠች ------------------------
4. የለታ ረጅም ሱሪ ------------------------------
5. ጥንት ------------------------------------------
6. በመሰላሉ ላይ ----------------------------------
7. የሰው ልጅ ከዋክብትን ያደነንቃል -----------
8. ባለ ጥቁር ላባ ወፍ ----------------------------
9. ቢራቢሮ ከረባት --------------------------------
10. ኮከብ -----------------------------------------

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

### 1. ልቦለድ

ልቦለድ ስነፅሁፍ ደራሲው በገሃዱ ዓለም እውነት ላይ ተመርኩዞ ከአፅምሮው እያመነጨ፣ ውበት ባለው ቋንቋ አቀናብሮ የሚያዘጋጀው የፈጠራ ፅሁፍ ነው። ለዚህም አጭር ልቦለድና ረጅም ልቦለድ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

### 1.1 የልቦለድ አላባውያን

የልቦለድ አላባውያን ወይም ፍሬ ነገሮች በመባል የሚታወቁት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው። እነሱም፡- ገፀባህርይ፣ መቼት፣ጭብጥ፣ሴራ፣ ግጭት፣ ምልሰት፣ ንግርት ሲሆኑ፡-

ሀ/ ገፀባህርይ፡- በልቦለድ ፅሁፍ ደራሲ ከሃሳቡ አመንጭቶ የሚፈጥራቸው የገሃዱን ዓለም እውነታ የሚወክሉ ፍጡሮች ናቸው፡፡

ለ/ መቼት፡- መቼ? እና የት? ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ነው፡፡ የልቦለዱ ታሪክ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ ማለት ነው፡፡

ሐ/ ጭብጥ፡- በልቦለዱ የሚተላለፈው መልዕክት ማለት ነው፡፡

መ/ ግጭት፡- አንዱ ገፀባህርይ ከሌላው ገፀባህርይ ጋር የሚፈጥረው ንትርክ፣ ገፀባህርያት ይህንን ልፈፅም ወይስ አልፈፅም ብለው ከራሳቸው ሀሳብ የሚያደርጉት ሙጉት፣ እንዲሁም ገፀባህርያት ከተፈጥሮ ሁኔታዎች ጋር የሚፈጥሩት ቅራኔ ነው፡፡

ሠ/ ሴራ፡- በምክንያትና በውጤት የተጣመረና በግጭት የተሞላ የድርጊቶች ቅደምተከተል ነው፡፡

ረ/ ምልሰት፡- በልቦለድ ድርሰት ያለፈ ታሪክን በትዝታ መልክ ማቅረብ ነው፡፡

ሰ/ ንግርት፡- ገፀባህርይ ለወደፊቱ ሊገጥመው የሚችለውን ነገር አስቀድሞ ፍንጭ ወይም ጥቆማ መስጠት ነው፡፡

## አያ ጥበቡ (አጭር ልቦለድ)

አቶ ጥበቡ የሚባሉ አንድ አዛውንት ነበሩ፡፡ በእለተ ቅዳሜ ረፋድ ላይ ወደ እርሻቸው ደፋ ቀና እያሉ ሲሄዱ አንዲት መልከ መልካም ሴት ከመንገድ ዳር ቁጭ ብላ ስታለቅስ ያገኟሉ፡፡ “ምነው ልጄ፣አንችን የመሰለች ቆንጆ ይስቃል፣ይጫወታል እንጂ፤እንዴት ሆደ ባሻ ይመስል ዝምብሎ መንገድ ላይ ያለቅሳል?” ሲሉ ይጠይቋታል፡፡ እሷም “አባቴ የማለቅሰው ዝም ብዬ ሳይሆን፣”እግረ ቀጭን እንደ እንስሳ፣ልበሙሉ እንደ አንበሳ” እያለ ጧት ማታ ራሱን የሚያሞካሽ እኔን ሲሻው “አቅመቢስ” ሲሻው “ቀልበቢስ!” እያለ የሚያናንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ባል አጋጥሞኝ ሆድ ቢብሰኝ ነው” ተለዋለች፡፡ እሳቸውም “ወቼው ጉድ! እግሩ ቢቀጥን፣ ልቡ ቢደነድን፣ ከእንስሳና ከአንበሳ የተወለደ

መሰለው? ከሴት ማህፀን አይደለም የወጣው? ወይ አለማወቅ ደፋር! ተይው! እያደር ልብ ሲገዛ ይተወዋል፡፡ እስከዛው ትንሽ ሆደ ሰፊ መሆን ጥሩ ነው ልጄ!"

አሏት፡፡ እስዋም እንባዋን ጥርግ ጥርግ አድርጋ ተነሳችና ቀስ እያለች ወደ ቤቷ ታዘግም ጀመረች፡፡

(ምንጭ፡- ባዬ ይማም፣ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፤2002፡ ለመማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

## ተግባር አንድ

**ሀ/ ከላይ "እያ ጥበቡ" የሚል አጭር ልቦለድ ቀርቦላችኋል፡፡ ልቦለዱን ካነበባችሁ በኋላ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በተጠየቃችሁት መሰረት መልሱ፡፡**

1. በልቦለዱ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያትን ዘርዝሩ፡፡ ዋና ዋናዎቹ ገፀባህርያትስ ማን ማን ናቸው፡፡
2. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ በየተራ ታሪኩን በቃል ተረኩ፡፡ እርስ በርስም ስህተቶቻችሁን ተራረሙ፡፡

3.የልቦለዱን መቼት ግለፁ፡፡

4. በቀረበዉ ልቦለድ ውስጥ ግጭት አለ? ካለ አብራሩ፡፡

5.አንድ አጭር ልቦለድ አንብባችሁ በራሳችሁ አባባል ፅፋችሁ ለክፍል በማቅረብ ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በመነሻም የሚና ጨዋታን ተመልክተናል፤ በመቀጠል የስኬት መንገዶችን ያየን ሲሆን የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላትንም በተገቢው መንገድ አይተናል፡፡ እንዲሁም የሀረግና የዓረፍተነገር ልዩነቶችን በምሳሌ ጭምር ያየን ሲሆን የልቦለድ አላባውያንን፡- ገፀባህርይ፣ መቼት፣ ጭብጥ፣ ግጭት፣ ሴራ፣ ምልሰትንና ንግርትን አንድ በአንድ በተገቢ ሁኔታ ተመልክተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከስኬት መንገዶች ውስጥ ሶስቱን ጥቀሱ።
2. የሚና ጨዋታ ማለት ምን ማለት ነው?
3. በቃል፣ በሀረግና በዓረፍተ-ነገር መካከል ልዩነት አለ? ካለ ከነምሳሌው ግለፁ::
4. የልቦለድ አላባውያን የሚባሉትን ዘርዝሩ።
5. ከታች በቀረቡት ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ ፍቻቸውን በሚያሳይ መልኩ ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው።

   ሀ/ ይገባል

   ለ/ ቁርስ

   ሐ/ እንስራ

   መ/ ይጠባል

   ሠ/ አለ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሚና ጫዋታ ሂደትን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የሐረግና ዓረፍተ-ነገር ልዩነቶችን መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የልቦለድ አላባዊያንን ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 4 | የስኬት መንገዶችን መግለፅ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ለተሰጡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የሕይወት ታሪክ

### የምዕራፉ አበይት ዓላማዎች:-

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- በድምፅ የተቀረፀ የተለያዩ ታሪኮችን ታዳምጣላችሁ፡፡
- ሱስ በሚያሲይዙ ነገሮች ዙሪያ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- የታዋቂ ግለሰቦችና የራሳችሁን የህይወት ታሪክ ትፅፋላችሁ፡፡
- ከውስብስብ ቃላት ነጠላ ቃላትን ታወጣላችሁ፡፡
- የተዘበራረቁ ቃላትን በማስተካከል ዓረፍተ-ነገር ትፅፋላችሁ፡፡
- የተለያዩ እንቆቅልሾችን ሰብስበው በመጠያየቅ ትፅፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህሩ/ርቷ ስለ "ዓባይ ግድብ" የተቀረፀ አጭር ታሪክ ያስደምጧቿዋል፡፡ በጥሞና አድምጣችሁ ሀሳቡ ላይ ተወያዩ፡፡

ለ/ የ "ሀይሌ ፊዳ" የህይወት ታሪክ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ሲነበብላችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ ለሚቀርብላችሁ ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ ስጡ፡፡

1. የሀይሌ ፊዳ የትውልድ ቦታ የት ነው?

2. ሀይሌ ፊዳ ወደ ፓሪስ ለትምህርት የሄደው በስንት ዓመተ ምህረት ነው?

3. በቀረበው ታሪክ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዊንጌት ትምህርት ቤት ትምህርቱን ያጠናቀቀው ማን ነው?

4. ሀይሌ ከታሪኩ ባዳመጣችሁት መሰረት በትምህርት ዘመኑ የሚታወቀው በምንድን ነው?

5. የሀይሌ ምኞት ምን ነበር?

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ

1. ሱስ ሊያስይዙ የሚችሉ ነገሮችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

2. በተለያዩ ሱሶች ወይም አደንዛዥ ዕፆች የተጠመዱ ወይም የተያዙ ሰዎችን ባህሪ ከወላጆቻችሁ በመጠየቅ ያገኛችሁትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

3. ከታች በቀረቡት ሳጥኖች ውስጥ በሱስ ወይም አደንዛዥ ዕፅ ምክንያት ሊመጣ የሚችል ጉዳት ላይ በጥንድ ሀሳብ በመለዋወጥ የተማመናችሁበትን ሀሳብ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡-

| ጫት | ሲጋራ | መጠጥ |
|---|---|---|
| አዕምሮን ያደነዝዛል | ሳንባን ይጎዳል | ጉበትን ይጎዳል |
| | | |
| | | |
| | | |

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

ቅድመ ንባብ ጥያቄ፡-

1. የህይወት ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የህይወት ታሪክ በስንት መንገድ ሊፃፍ ይችላል?
3. ታዋቂ የምትሏቸው ሰዎች አሉ? ምሳሌ ጥቀሱ፡፡

### ድምጻዊ ሃጫሉ ሁንዴሳ

ሃጫሉ ሁንዴሳ ተወልዶ ያደገው ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ርቃ በምተገኘው አምቦ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ እናቱ ወይዘሮ ጉደቱ ሆራ፣ ሃጫሉ ከልጅነቱ ታሪክን የመስማት፣ የመንገር፣ ዝንባሌውንና ችሎታውን ጠንቅቀው ተረድተውት ስለነበር ከመጀመሪያው አንስቶ ያበረታቱት እንደነበር በተደጋጋሚ ሃጫሉ ያስታውሳል፡፡

አባቱ አቶ ሁንዴሳ ቦንሳ ደግሞ ልጃቸው ሃጫሉ በትምህርቱ ዓለም ገፍቶ ዶክተር ወይም የዩኒቨርሲቲ መምህር እንዲሆንላቸው ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው፡፡ ሃጫሉ ግን ገና ከልጅነቱ ጀምሮ በፍቅሯ ለወደቀላት ሙዚቃ ነበር መላው ትኩረቱ፡፡ በአስራዎቹ እድሜው ላይ እያለ እንኳን የበርካቶችን ስሜት የሚኮረኩሩ ሙዚቃዎችን ይጫወት ነበር፡፡

ሃጫሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለ በ1998 ዓ.ም በቁጥጥር ስር ውሎ ለአምስት ዓመታትም አምቦ በሚገኘው እስር ቤት አሳልፏል፡፡ ፖለቲካዊ መልዕክት ያላቸውና ተወዳጅ የኦሮሞ የትግል ሙዚቃዎችን ማቀንቀኑን እንዲያቆም ለማድረግ መታሰሩን ሃጫሉ ይናገራል፡፡ ነገር ግን መታሰሩ እንደውም ይበልጥ በሥራው እንዲገፋበትና በሰዎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እና ጭቆና የበለጠ እንዲገባው ማድረጉን በአንድ ወቅት ተናግሮ ነበር፡፡ የሙዚቃ ግጥሞችን መጻፍና ሙዚቃ ማቀናበር የተማረው በእስር ላይ እያለ ነበር፡፡ ከአምስት ዓመታት በኋላ ሲለቀቅ የደረሰበትን በደል ለመቃወምና ለሚሊዮኖች ድምጽ ለመሆን ወስኖ እንደወጣ ሃጫሉ ይናገራል፡፡

በአጭር ጊዜም በኦሮምኛ ተናጋሪው ሕዝብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በመላዋ አገሪቱ ተወዳጅ የሆነለትን 'ሰኚ ሞቲ' የተሰኘውን አልበሙን አቀረበ፡፡ የዚህ የሙዚቃ ስብስብ አብዛኛዎቹ ግጥሞችና ዜማዎች ሃጫሉ በእስር ላይ እያለ የሰራቸው እንደነበሩ ይነገራል፡፡

በወቅቱ በሃያዎቹ መጀመሪያ የእድሜ ክልል ውስጥ የነበረው ሃጫሉም በዚህ አልበሙ በተለይ ደግሞ የአልበሙ መጠሪያ በነበረው ሙዚቃው ቋንቋውን በማይችሉ ሰዎች ዘንድም ታዋቂነትን ለማትረፍ ችሎ ነበር፡፡

ከጥቂት ዓመት በኋላም ወደ አሜሪካ የሙዚቃ ሥራዎቹን ለማቅረብ በሄደበት ጊዜ ሁለተኛውንና "ዋኤ ኬኛ" አልያም "የእኛ ነገር" የሚል ትርጉም ያለውን አልበሙን ለቀቀ፡፡ በወቅቱ አልበሙ አማዞን ላይ በከፍተኛ ሁኔታ በመሸጥ ከፍተኛ ትኩረትን አግኝቶ የነበረ ሲሆን፤ የሃጫሉ ተወዳጅነትም የበለጠ እየተጠናከረ መጣ፡፡ ሃጫሉ ተወዳጅ የሆኑ የኦሮሞ የሙዚቃ ስልቶችን ከዘመናዊው ሙዚቃ ጋር በማጣመር በሚያቀርባቸው ሥራዎቹ የብዙዎችን ጆሮና ቀልብ ለመማረክ አስችሎታል፡፡

በአገሪቱ የሚገኙ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችም ሙዚቃዎቹን በተደጋጋሚ በማጫወታቸው በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ አድናቆትን ማግኘት ችሏል፡፡ ከሦስት ዓመት በፊት በአገሪቱ ተቀስቅሶ ከነበረው ጸረ መንግሥት ተቃውሞ ጋር በተያያዘ በተለይ በኦሮሚያ ክልል ሲካሄድ በነበረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ወቅት ሃጫሉ ያወጣው 'ማላን ጂራ' የተሰኘው ነጠላ ሙዚቃው ከፍተኛ ተወዳጅነትን ከማትረፍ አልፎ የእንቅስቃሴው መነቃቂያ ሆኖ ነበር፡፡

ሃጫሉ የመንግሥት ባለስልጣናት በሚገኙባቸውና በቀጥታ በቴሌቪዥን በሚቀርቡ በትልልቅ የሙዚቃ መድረኮች ላይ በመገኘት ሙዚቃዎቹን በሚያቀርብበት ጊዜ ያለፍርሃት የሚሰማውን ፖለቲካዊ ጉዳዮችንም በማቅረብ በድፍረቱ ይታወቃል። ባለትዳርና የሦስት ልጆች አባት የነበረው የ36 ዓመቱ ድምጻዊ ሃጫሉ ሁንዴሳ ሰኞ ሰኔ 22/2012 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተፈጸመበት ጥቃት ህይወቱ አልፏል።

(ምንጭ፡- “Qaalii” የኦሮሞ ታጋይ አርቲስቶች ታሪክ በአብሲ ፍሌ እና በቀለ ለታ በ2013ዓ.ም ከታተመ የኦሮምኛ መፅሐፍ ተተርጉሞ የተወሰደ(15-18)።)

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን በማንበብ ትክክል የሆነዉን ሀሳብ <u>እዉነት</u> ትክክል ያልሆነዉን ደግሞ <u>ሀሰት</u> በማለት በቃል መልሱ።

1. ባለታሪኩ በህዝብ ዘንድ የሚታወቀው በስፖርት ዝነኛ በመሆኑ ነው።
2. ሀጫሉ ተወልዶ ያደገው በአንቦ ከተማ ውስጥ ነው።
3. ታሪኩ ላይ የተገለፀው ግለሰብ የአካባቢና የቤተሰብ ጫና ተቋቁሞ የፈለገበት ቦታ መድረስ ችሏል።
4. የሀጫሉ አባት ምኞት ልጃቸው ዶክተር እንዲሆንላቸው ነበር።
5. ሀጫሉ የተወለደው በ1988ዓ.ም ነው።

ለ/ ከታች የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ተመሳሳያቸውን ከ "ለ" ረድፍ በመፈለግ አዛምድ/ጂ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ትኩረት | ሀ/ እንዲቀጥል |
| 2. በርካታ | ለ/ መቃረን |
| 3. እንዲገፋበት | ሐ/ አፅንኦት |
| 4. ማቀናበር | መ/ ዝነኛ |
| 5. ተወዳጅ | ሠ/ ብዙ |
| 6. መቃወም | ረ/ በጊዜው |
| 7. ታዋቂ | ሰ/ ማስደሰት |
| 8. በወቅቱ | ሸ/ ማቀናጀት |
| 9. መማረክ | ቀ/ ተፈላጊ |

## ክፍል አራት:- መፃፍ

### ➢ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ

የህይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል። እነሱም:- የራስ የህይወት ታሪክና የግለሰብ የህይወት ታሪክ ናቸው።

የህይወት ታሪክ ሲፃፍ መካተት ያለበት :-

- ስም እስከ አያት መፃፍ
- የትውልድ ስፍራና የትውልድ ዘመን
- ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መፃፍ
- የትምህርት ደረጃን መግለፅ
- የፈፀማቸውን ጉልህ ተግባሮች፣አስተዋፅኦ በቅደም ተከተል መዘርዘር
- አሁን ላይ የደረሰበት ደረጃ መፃፍ
- ቀላልና ግልፅ የሆነ ቋንቋን መጠቀም

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ግለ ታሪካችሁን በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ለ/ ቀጥለው ስማቸው ከተጠቀሱት ታዋቂ ግለሰቦች መካከል አንዱን በመምረጥ የህይወት ታሪካቸውን ጠይቃችሁ በመፃፍ ለክፍላችሁ ተማሪዎች በንባብ አሰሙ፡፡ ከተነበበው ታሪክ የወሰዳችሁትን ተሞክሮ በቃል ተናገሩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ጄ/ዋቆ ጉቱ | አበበች ጎበና | አስተር ገኖ |
| ጄ/ታደሰ ብሩ | ባሮ ቱምሳ | ደራርቱ ቱሉ |
| ዶ/ር ሀይሌ ፊዳ | ኤሌሞ ቂልጡ | ጥሩነሽ ድባባ |

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተግባር አንድ

**ዉስብስብ ቃላት**

ከአንድ ቃል የተለያዩ ቃላትን መመስረት

ምሳሌ፡- አለመደጋገም-----------አለመ፣ ደጋገመ፣ አለ

ነገሰችባቸው---------------ነገሰ፣ ነገ፣ ገሰገሰ፣ ሰባ

ሀ/ ከላይ በቀረቡት ምሳሌ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ለይታችሁ ፃፉ፡፡

1. ድብልቅልቅ-------
2. አፈራረሰችው-----
3. አለማመንታት----
4. ያለብሳቸዋል--------

ለ/ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጎች በቃል ፍቺ ስጡ፡፡

1. መመራመር
2. ተማሪ
3. ረበሸ
4. ቋሚ
5. መቆጨት

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ቃላት አስተካክላችሁ ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡

- ምሳሌ፡- ሲና አንደኛ ተማሪዎች ከክፍሉ ወጣች
- ሲና ከክፍሉ ተማሪዎች አንደኛ ወጣች፡፡

1. ነው አለቃ ብልሱማ የክፍሉ
2. ናፍያድ ሄደች ቡራዩ ወደ ትናንትና
3. ነው የእድገት ትምህርት መሰረት
4. የስንፍና ማርፈድ ነው ምልክት
5. መስላል ነው ትምህርት የእውቀት
6. መፅሐፉን የአማርኛ ወሰደው ማን
7. ሪሐና መጣች መቼ ከገበያ
8. በህዳር የኤድስ ቀን የዓለም ይከበራል ወር
9. ያውቃል ብዙ ነገር ለሜሳ
10. ሴቶች እንጂ እድል አላጡም ችሎታ

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

እንቆቅልሽ ከስነቃል ክፍል የሚመደብ የመልዕክት ማስተላለፍያ አንድ ቅርፅ ነው፡፡ እንቆቅልሽ ተምሳሌታዊ የአቀራረብ ስልት ይከተላል፡፡ አቀራረቡም በጥያቄ መልክ ሲሆን ጠያቂና ተጠያቂ የሚመላለሱበት ልማድም ውበት አለው፡፡ ጥያቄውን በጥሞና በማስተዋል ትክክለኛውን መልስ ወይም ፍቺ ለማግኘት አዕምሮን በሚገባ ማሰራትና የተለያዩ ነገሮችን ባህርያት በተዛምዶ መመርመርን ይጠይቃል፡፡ እንቆቅልሽ እንደ ሌሎች የስነቃል ዘርፎች እንደ ተረትተረት፣ እሰጥ እገባና ሌሎች ሁሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ የስነ-ቃል ዓይነት ነው፡፡

ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ይበልጥ ህፃናትና ወጣቶች የማሰብ ወይም የማስተዋል ችሎታቸውን ይመዝኑበታል፡፡ አዕምሮአቸውን በማነሳሳትና የውድድሩ አሸናፊ ለመሆን በስሜትና በንቃት የሚሳተፉበት የቋንቋ ፈርጥ( ዋና) ሆኖ የኖረ የሀሳብ መግለጫ ስልት ነው፡፡ የማገናዘብና የማስተዋል ችሎታና ብቃት የሚዳብርበት ጠቃሚ የህፃናትና ወጣቶች መግባቢያ ስለሆነ ችላ ባይባል ጥሩ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ጠያቂ፡ እንቆቅልህ/ሽ

መላሽ፡ ምን አውቅልህ/ሽ

ጠያቂ፡ ሲመሽ ወደ ዉጪ ሲነጋ ወደ ቤት

መላሽ፡ በር

## ተግባር አንድ

### ሀ/ ከታች የቀረቡትን እንቆቅልሾች ተራ በተራ ተጠያየቁ፡፡

1. የአፋፉ ላይ ጎጆ በሩ ሁለት ነው፡፡
2. ትንሽ እንስሳ ተልባ ለብሳ፡፡
3. ሲሄድ ሲሄድ ውሎ እራቱ ጥሬ፡፡
4. ውሃ ፈሪ ፀሃይ ደፋሪ፡፡
5. ቀን ተሸልማ ሌት የምትራቆት፡፡
6. ወተቷ ይጠጣ ስጋዋ አይበላ፡፡
7. ጥቁር ፈረስ ቼ! ቢሉት አይመለስ፡፡
8. ለምጣጭ በቆንጣጭ፡፡
9. ሰው መሳይ ተሰቃይ፡፡
10. አፍንጫ እያላት የማትናፈጥ፡፡

### ለ/ በአካባቢያችሁ አዘውትረው የሚነገሩ እንቆቅልሾችን ጠይቃችሁ በመምጣት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተጠያየቁ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የማድመጥ ክሂል ላይ ብዙ ተግባራትን በመስራት ልናዳብር ችለናል፡፡ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ ምንነትንም ከነ አፃፃፍ መመሪያው በማወቅ የተለያዩ ታዋቂ ግለሰቦች ታሪክን በማድመጥ የየተሞክሮአቸውን በሰፊው ለማየት ሞክረናል፡፡

የሱስ አስከፊነትንም በመናገር ክሂል ላይ አንስተን ተወያይተንም የሚያስከትሉትን ችግሮችንም ለይተን በማወቅ መጠንቀቅ እንዳለብን ተገንዝበናል፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችንም ለቃላት ፍቺን በመስጠት ተግባራትን ለመስራት ችለናል፡፡ በሰዋስው ክፍል ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን በማስተካከል ዓረፍተ-ነገርን አቀናጅተን በመፃፍ የተስተካከለውን በማንበብ ማስተካከያ ወስደናል፡፡ በምዕራፉ የመጨረሻ ክፍል በሆነው ስነፅሁፍም የእንቆቅልሽ ምንነትና የአከዋወን ዘዴን በማወቅ በመጠያየቅ አዕምሮአችንን የምናዝናናበት መንገድ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ/ ከታች ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች በተጠየቃችሁት መሰረት መልሱ፡፡

1. የህይወት ታሪክን በስንት መንገድ እንከፍላለን?
2. ሱስ ከሚያስይዙ ነገሮች እንዴት መራቅ እንችላለን ተወያዩበት፡፡
3. አዕምሮን ጂምናስትክ የምናሰራበት መንገድና ጠያቂና ተጠያቂ የሚያስፈልገው በስነ ቃል አይነት ውስጥ የሚመደበው ማን ነው?

ለ/ ከታች ከቀረቡት ቃላት ውስብስብ የሆኑ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ፡፡

- ነጎደ
- አሰባሰበ
- አርበኛ
- ተደበላለቀ
- አስጠራቻው
- ለየ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳክሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀለበውን የህይወት ታሪክ ፅንሰ ሀሳቡን መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የሱስ ምንነትና ጉዳትን ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የህይወት ታሪክ አፃፃፍን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ስለ ውስብስብ ቃላት መግለፅ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ለቀረቡት እንቆቅልሾች ምላሽ መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(? ) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# የአየር ንብረት

## የምዕራፉ አበይት ዓላማዎች:-

ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-

- ስለ መልካምነት መሰረት ያደረገ ፅሁፍን ታዳምጣላችሁ።
- ካርታና ሰንጠረዥን ተጠቅማችሁ የተለያዩ መረጃዎችን ትናገራላችሁ።
- የንባብ መመሪያዎችን በመከተል ምንባብ ታነባላችሁ።
- ጅምር ታሪክን አሟልታችሁ ትፅፋላችሁ።
- ለቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- የአፈ-ታሪክንና የተረት ተረትን ምንነት ትገልፃላችሁ።
- ከግሳዊ ሐረግ የተመሰረቱ ሐረጎችን ትለያላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

ሀ/ መምህሩ/ቷ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን "መልካሙን ሁሉ እንፈፅም" የሚል ምንባብ አድምጣችሁ ለሚትጠየቁ ጥያቄ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. መልካም የሚለው ቃል የሚወክለው ምንን ነው?
2. በዚህ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የግብረ ገብ ትምህርት ያስፈልጋል ትላላችሁ? ለምን?
3. ሙሰኞችንና ቀማኞችን አንድ በሚያደርጋቸውና በሚለያያቸው ነገሮች ላይ ተወያዩ፡፡
4. መልካም ነገር ከመፈፀማችን በፊት በአስተሳሰባችን መልካሙን ማሰብ ይገባናል ስል ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ተናገሩ፡፡

ለ/ ያዳመጣችሁት ምንባብ ግብረገብነትን የሚያሳይ ነገር ነው? አዎን ካላችሁ ከምን ከምን አንፃር ነው? ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. በኢትዮጲያ ሞቃታማ አካባቢዎችን ከተለያዩ ባለሙያዎች በመጠየቅ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
2. በኢትዮጲያ ደጋማ የአየር ንብረት ያለባቸው ቦታዎች ባለሙያዎችን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለው ጉዳት ምን ምን ናቸው?

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፡

1. የአየር ጠባይ ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. የአየር ብክለትና የአየር ንብረት መካከል ልዩነት አለ? ካለ ተናገሩ፡፡
3. የአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰተው በምን ምክንያት ነው?

## የአየር ንብረት ለውጥና ችግሮቹ

በአካባቢያችሁ የአየር ንብረት ለውጥ እንዳይከሰት ምን መደረግ አለበት?

የአየር ሁኔታ ማለት፡- በቀኑ በሳምንቱ የተመዘገበ የሙቀት፣ የዳመና፣ የዝናብ፣ የንፋስ፣ የቅዝቃዜ፣ ወዘተ.ሁኔታዎችን ለመግለጽ የምንጠቀምበት አገላለጽ ነው፡፡

የአየር ንብረት ማለት፡- በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ የአየር ሙቀት፣ የዝናብ መጠን፣ የአየር እርጥበት፣ የንፋስ ፍጥነት ወዘተ. የመሳሰሉትን አማካይ ውጤት ነው ፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ፡- ለበርካታ ዓመታት የተመዘገበ የአየር ንብረት አማካይ ጥቅል ውጤት መቀየርን የሚያመለክት ነው፡፡ በአጭሩ ለረዥም ዓመታት የተመዘገቡ አጠቃላይ የእርጥበት፣ የቅዝቃዜ፣ የሙቀት፣ የነፋስ አቅጣጫ፣ የአየር ግፊት፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ባህሪያት መለወጥ ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ በረጂም ጊዜ የሚከሰት ነው ፡፡ ሰፊ መልክዓ ምድራዊ ሽፋንም ያለው ነው፡፡ በሌላ በኩል የአየር ጠባይ ለውጥ የምንለው በቀናትና በወራት የሚቀያየር የንፋስ፣ የዝናብ ፣ የሙቀትና፣ የቅዝቃዜ፣ ለውጥ ሲሆን ለውጡም የሚገለጸው በአነስተኛ መልክዓ ምድር ላይ ነው ፡፡

በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ማጤን በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶቹ በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ሙቀት አማቂ ጋዞች ከመጠን በላይ መከማቸታቸው ነው፡፡ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ክምችት ያባባሰውና ለአየር ንብረት ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው የሰው ልጅ የድንጋይ ከሰልን፣ የተፈጥሮ ነዳጅና ጋዝን በሰፊው በመጠቀሙ ምክንያት ካርቦን ዳይኦክሳይድ የተሰኘውን ጋዝ ወደ አየር በመልቀቅ ቀድሞ የነበረውን የአካባቢ አየር ተፈጥሮአዊ ሁኔታ እንዲዛባ

ምክንያት በመሆኑ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሰውን ልጅ አሁን እየገጠመው ያለው ፈተና በሰው ሰራሽ ምክንያት በአካባቢ አየር ውስጥ ባሉት የሙቀት አማቂ ጋዞች ለውጥ ሳቢያ በተከተለው አየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሱ የተለያዩ አደጋዎች ናቸው፡፡

ይህ ማለት ግን ተፈጥሮም በራሷ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ አታደርግም ማለት አይደለም፡፡ እንደ እሳተ ገሞራና ተፈጥሯዊ የሰደድ እሳትም ለአየር ንብረት ለውጡ አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው ፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው አደጋዎች ድንበር ተሻጋሪ ናቸው፡፡ ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሆኑ ክስተቶች በተከሰቱበት አካባቢ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆን ድንበር ተሻጋሪ ናቸው ፡፡

በዚህ ምክንያት ነው ለአየር ንብረት ለውጥ ብዙም ድርሻ የሌለን የታዳጊ አገራት ህዝቦች የበለጸጉ አገራት ሲያከማቹ በኖሩት የሙቀት አማቂ ጋዞች ጥርቅም ሳቢያ በተከተለው የአየር ንብረት ለውጥ ይበልጥ ተጎጂ ለመሆን የበቃነው ፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ዋናዋና ችግሮች፡-

### ሀ/ የግብርና መሬት መቀነስ

የሀገራችን አብዛኛው ህዝቧ በግብርና የሚተዳደር መሆኑ ይታወቃል፡፡ የህዝቧም ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ የህዝብ ቁጥር መጨመር ተጨማሪ የምግብ አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው፡፡ የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አካባቢ ላይ ተፅዕኖ ማድረሱ የማይቀር ነው ፡፡ በዚህ ምክንያት በአካባቢ ላይ ጫና ሲደርስ የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ሊቀንስና ቁጥሩ እያደገ የሚገኘውን ህዝብም መመገብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

### ለ/ የመሬት መከላት፡-

የኢትዮጵያ መልክዓ - ምድራዊ አቀማመጥ ተራራ፣ ኮረብታማ፣ እንዲሁም ዝቅተኛ በታዎችና ሜዳዎች የሚበዛበት ነው፡፡ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች መነሻቸው ከደጋማው አካባቢ ነው፡፡ የመሬቱ አቀማመጥ ከወንዞች የፍሰት አቅጣጫ ጋር ተዳምሮ ለአፈር መከላት የተመቸ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት አፈሯ እየታጠበ ወደ ጎረቤት ሃገር መጓጓዙ የተለመደ ሆኗል፡፡ ለአፈር መከላት ዋናው ምክንያት የወራጅ ውሃ እና በደረቅ ወቅትና በሞቃታማው አካባቢ የሚከተለው አውሎ ንፋስ ነው፡፡ ይህም የአየር ንብረት ለውጥን ከማባባሱም በተጨማሪ የድርቅ መከሰትን የበረሃማነት መስፋፋት፣ የግብርና ምርት መቀነስ፣ የተፈጥሮ ሚዛን መቃወስና የመሳሳሉትን አስከትሏል፡፡

### ሐ/ የሰውና የእንስሳት ጤና

የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥረው የጤናችግር በሰው ዘር ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ እንደ ሰው ልጅ ሁሉ የቤትና የዱር እንስሳትም የአየር ንብረት ለውጥ በሚፈጥረው የጤና ችግር ተጠቂዎች ናቸው፡፡ አሁን አሁን ደግሞ በቆላማውና በበረሃማው የአገራችን ክፍል ተወስነው የነበሩት በሽታዎች ወደ ደጋው በመሸጋገር ችግር በመፍጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ፡- ወባና የገንዲ በሽታ ተጠቃሽ ናቸው ፡፡

የአየር ንብረት ለውጡ እየተባባሰ በሄደ ቁጥር የበሽታዎቹ የመስፋፋት አቀም የበለጠ ይጨምራል፡፡ አዳዲሶቹም የመከሰት እድላቸው ይሰፋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፡- እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ይቀንሳሉ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬም ሆነ የሃገር ውስጥ ፍጆታ አቅርቦት አናሳ ይሆናል፡፡

### መ/ የገፀ- ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ መጠን መቀነስ

ውሃ ህይወት ነው፡፡ ዓለማችን ከ75% በላይ የሚሆነው መሬት በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አስተማማኝ በሆነ የተፈጥሮ ዑደት አማካኝነት መጠኑ እንደተጠበቀ እንዲቆይ ተፈጥሮ ግድ ትላለች ፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች ውሃ በመባከኑና የጥራት ይዘቱን በማጣቱ ሳቢያ የንፁህ ውሃ አቅርቦት እጥረት በብዛት ያጋጥማል፡፡ በተለይ በአንዳንድ የኢትዮጵያ ከተሞች ችግሩ ጎልቶ ይታያል፡፡ የውሃ መጠን ማነስና የጥራት መጓደል የሰብል ምርትንና ብዝሃ ሕይወትን ይጎዳል፡፡

ሃገራችን ይበልጥ እየጎዳት የሚገኘው የኢኮኖሚ አቅማችን አናሳ በመሆኑና ትላልቅ ወንዞችን ጠልፎ የመጠጥ ውሃ ማቅረብ አለመቻሉ ነው። "የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው" የሚለው አባባልም ከዚህ የመነጨ ይመስላል ። በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ በሃገር የኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ጉልህ የሆነ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ማህበራዊ ችግሮችን በማባባስ አለመረጋጋትን፣ ስደትን፣ ረሃብና ጦርነትን የመሳሰሉትን ሁነቶች ሊያባብሳቸው ይችላል።(ምንጭ፡-ANRS: Environoment, Forest, and Wild Life Protection and Development Authority.)

## ተግባር አንድ

### ሀ/ የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። በምንባቡ መሰረት ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ትክክለኛውን ምረጡ።

1.በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ የአየር መለዋወጥ ሁኔታ -------በመባል ይታወቃል።

ሀ/ የአየር ሁኔታ ለ/ የአየር ንብረት

ሐ/ የአየር ብክለት መ/ ሜትሮሎጂ

2. ለአየር ንብረት ለውጥ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሰው------------ነው።

ሀ/ የአማቂ ጋዞች ከበቂ በላይ መከማቸት

ለ/ የተፈጥሮ ሁኔታ

ሐ/ የደን መጨፍጨፍ

መ/ ሁሉም መልስ ናቸው

3. የአየር ለውጥ አደጋዎች ድንበር ተሻጋሪ ናቸው።

ሀ/ እውነት ለ/ ሀሰት

4. ከሚከተሉት መካከል አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

ሀ/ የመሬት መከላት ለ/ የሰውና የእንስሳት ጤና

ሐ/ ንፁህና አመቺ የአየር ሁኔታ መ/ ሀ ና ለ መልስ ናቸው

5. ----------በቀኑ፣ በሳምንት የተመዘገበ የሙቀት. የዳመና፣ የንፋስ ወዘተ. ሁኔታዎችን ለመግለፅ የምንጠቀምበት አገላለፅ ነው፡፡

ሀ/ የአየር ንብረት ለ/ አየር

ሐ/ የአየር ሁኔታ መ/ የአየር ንብረት ችግር

6. በአለማችን ከ75% በላይ የሚሆነው መሬት በምን የተሸፈነ ነው?

ሀ/ ውሃ ለ/ የድንጋይ ከሰል

ሐ ደን መ/ መልስ የለውም

## ለ/ ሰንጠረዡ ውስጥ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የአየር ንብረት እና የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

| የአየር ንብረት | የአየር ንብረት ለውጥ ችግር |
|---|---|
| ምሳሌ፡-1. የዝናብ መጠን | ማህበራዊ ችግሮችን ማባባስ |
| 2. የንፋስ ፍጥነት | ረሃብና ጦርነት |
| 3. | |
| 4. | |
| 5. | |
| 6. | |

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ተግባር አንድ

ሀ/ ቀደም ባሉት ምዕራፍ ውስጥ ስለ አያያዥ ቃላት መማራችሁ ይታወሳል፡፡ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አስር ዓረፍተነገሮችን ከፃፉችሁ በኋላ የፃፉችኋቸውን ዓረፍተ ነገሮች ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

## ማስታወሻ

### ውጥን ታሪክን አሟልቶ መፃፍ

ውጥን ታሪክን ማሟላት ማለት ሀሳቡ ያላለቀውን ታሪክ በማሟላት ጨሪሶ መፃፍ ማለት ነው። አንድ ውጥን ታሪክ በተለያየ መንገድ ሊያልቅ ይችላል ነገር ግን ታሪኩ የሚያልቅበት መንገድ ታሪኩ ሲጀመር ከነበረው ሀሳብ ጋር መስማማት ይኖርበታል። ከጅምር ሀሳቡ የተለየ መሆን የለበትም።

ምሳሌ፡- የፋኖስ ብርጭቆና መብራት ባልና ሚስት ነበሩ። ብርሃንና ሰላም የሚባሉ ሁለት ወንድ ልጆችም ነበራቸው።

ከወንድማማችነታቸው ይልቅ ፍቅራቸው እጅግ ፅኑ ነበረ። እናትና አባታቸው በህግ ፀንተው አብረው ሲኖሩ መብራት እቤት ውስጥ ላለ ስራና ምግባቸውን ለማሰናዳት ዘወትር አትሰንፍም ነበር። የቤት ስራዋን ስትሰራ ለሚያዩዋት ሰዎች ሁሉ በጣም ደስ ታሰኝ ነበር። ስለሆነ በኑሮአቸው ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ትቆጣ ነበር። የፋኖስ ብርጭቆ ስራውን እየሰራ እየተወለወለ ብያምር ምቀኝነትና ቅናት መክረዋት ኖሮ እኔ ሁልጊዜ በስራ መቃተት አንተ መወልወልና ማማር ብቻ ብላ ስራ መያዙንና አለመያዙን በጊዜው መርምራ ሳታስብ ቀርታ በቁጣ ቃል እንዲህ አለችው…

| |
|---|
| የፋኖስ ብርጭቆና መብራት ታሪክ አላለቀም። በጅምር ያለ ታሪክ ነው፤ ይህንን ታሪክ በተለያዩ መንገዶች መጨረስ ይቻላል። ለምሳሌ፡- ታሪኩ ሊያልቅ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ የሚከተለው ነው፡- |

እኔን እንደ አንድ እስረኛ ባንተ ውስጥ አፍነህ፣ ሸፍነህ በዛም በዚህም እንደ ልቤ እንዳልስፋፋበት እየከለከልከኝ የምታኖረኝ ምን በደል ተገኝቶብኛል? ካንተ ውስጥ ብወጣ በውጪ ከዚህ ይበልጥ እንዳበራ አውቃለሁ። ካልተለያየን አይሆንልኝም አለችው።

ለ/ የሚከተለውን ጅምር ታሪክ አሟልታችሁ ፃፉ።በክረምት ወራት ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ የአካባቢያችን ልጆች ዋና ስራ ከብት ማገድ ነዉ። ከብቶችን የሚያግዱት ከመንደራችን ራቅ ብለዉ ከሚገኘዉ ሸለቆ ማዶ በተንጣለለው ሰፊ መስክ ላይ ነው። በአካባቢያችን ከባድ ዝናብ ከዘነበ ሸለቆ ይሞላል። ሸለቆው ሰፊስለሆነ ድልድይም ስለሌለ ከብቶችም ሆኑ ሰዎች መሻገር አይችሉም ። ስለዚህ ውሀእስኪቀንስ ይጠብቃሉ።…………………

## ክፍል አምስት ፡-ቃላት

### ሀ/ ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት የመዝገበ ቃላት ፍች ስጡና ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸሁ፡፡

ምሳሌ፡- ታረቁ ----እርቀሰላም አወረዱ

❖ ጥዋት የተጣሉ ሰዎች በሽማግሌ ታረቁ፡፡

ደግ---ቸር

❖ ጋዲሳ ደግ ልጅ ነው፡፡

1/ መመኘት

2/ ሰለቸ

3/ ምንጭ

4/ ብሩህ

5/ ተሰማ

6/ ታነፀ

7/ ችላአለ

8/ ነከረ

9/ አትኩሮት

10/ አእምዕሮ

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

**ሐረግ**

ሐረግ ፡- ቃላት እርስበእርስ በስርዓት በመቀናጀት የአንድ ዓረፍተ ነገር አካል ሆነው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ አንድ ሐረግ ምን አይነት ሐረግ እንደ ሆነ የሚወስነዉም በሐረጉ ዉስጥ መሪ ሆኖ የቀረበው ቃል በሚመደቡበት የቃል ክፍል ነው፡፡

ምሳሌ፡- በድንገት መጣ

- ዛሬ ሄደ
- ትምህርቱን ተማረ
- ልብሱን አጠበ

ከላይ የተጠቀሱት ግሳዊ ሐረግ ናቸው፡፡

## ተግባር አንድ

### ሀ/ ከላይ በቀረበው መግለጫና ምሳሌ መሰረት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ግሳዊ ሀረግን አስምሩበት፡፡

ምሳሌ፡- የዛሬው ብርድ በጣም አይሏል፡፡

1. ቶሎሳ ክፉኛ ታሟል፡፡
2. ያልሰራ ሰው ሁልጊዜ ይራባል፡፡
3. ኩማ በቅፅበት ወደቀ፡፡
4. ወንድሜን እንዲያጠና መከርኩት፡፡
5. ደራሲው ጥሩ ፅሁፍ ፃፈ፡፡

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

### ተረት

ተረት መተረት ከጀመረ ዘመን የለውም፡፡ ተረት የማውራት ውስጣዊ ስሜትና ተረት የማዳመጥ ፍላጎት ትረካን በስልጣኔ ታሪክ ውስጥ የሰው ልጅ የተፈጥሮ እኩያ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ተረት በድሮ ጊዜ ወይም ከእለታት አንድ ቀን በአንድ ቦታ እገሌና እገሌ የሚባሉ ሁለት ሰዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ እንዲህ ያለ ነገር ፈፀመ...እያለ የሚተርክና ወደፊት የሚጓዝ ትረካ ነው፡፡ የተረት ቅርፅና አቀራረብ ብዙ ባህሎች ተመሳሳይነት አለው፡፡ የአጀማመርና የአጨራረሱን ስርዓት ብቻ እንኳን ብናጤን ለዚህ አንድ ማስረጃ ልሆነን ይችላል፡፡ በሃገራችን በልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ዘንድ የተረትን አጀማመር ሲንመለከት የተባለውን በግልፅ እናያለን፡፡

ለምሳሌ፡-

በአማርኛ ተራቹ" ተረት ተረት" በማለት ተረቱን ሲጀምር

አድማጩ "የላም በረት" በማለት ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

ተራቹ ሲጨርስ" ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ" በማለት ይደመድማል፡፡

ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች ያለውን "ባሏ የሞተባት ሴት" የሚል ተረት አዳምጡ፡፡

## ባሏ የሞተባት ሴት

በአንድ ወቅት አንዲት ደስተኛ ሴት ነበረች፡፡ ባሏ ከመሞቱ በፊት የፈለገችሁ ሁሉ ተሟልቶላት ከልጆቿ ጋር ትኖር ነበር፡፡ ልጆቿም ደስተኞች ነበሩ፡፡ በኑሮአቸውም ደረጃ ባልና ሚስቱ የተከበሩ ነበሩ፡፡ ባሏ ከሞተ በኋላ ግን ሴትየዋን ኑሮ ከበዳት፡፡ ልጆቿም ደስታ እርቋቸው እናታቸውን እንዲህ በማለት ጠየቋት "ወደፊትስ እንዴት እንሆናለን?" እሷም "ልጆቼ ሆይ! ኑሮ ያለ አባት እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡ አባት ያለው ሁሉ ሰብሉ ቡቃያ ሲያወጣ ይደሰታል፡፡" አለቻቸው፡፡ ይህንንም ስትል ልጆቿ ክፉን ከደጉ በቀላሉ መለየት እንዲችሉ ለማለት ነው፡፡ ሁሉም ነገር ስታደርጉ ደስተኛና ነፃ ስለምትሆኑ ማንም አይጎዳችሁም፡፡ ክፉ ነገር ግን ማድረግ የለባችሁም፤ማንም አይረዳችሁምና፤ በዚህም ጊዜ ልጆቹ ካለ አባታቸው እርዳታ ጠንክረው መስራት እንዳለባቸው ተገነዘቡ፡፡ እናታቸውንም ስለተረዷት "የምትነግረን ሁሉ እውነት ነው፡፡ አሁን አባታችን ስለሞተ አስተማሪያችን እናታችን ናት" አሉ፡፡ በመጨረሻም " አሁን ቤታችንን ጥለን መሄድ አንችልም፡፡ እዚሁ ቆይተን ችግሮቻችንን በጋራ እንታገላለን፡፡" ብለው ወሰኑ፡፡

### ተግባር አንድ

ሀ/ ከላይ የተማራችሁትን የተረት ምንነትንና የአከዋወን ዘዴን በመጠቀም በአካባቢያችሁ የተለመዱ ተረቶችን ወላጆቻችሁን በመጠየቅ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩ፡፡

- **አፈታሪክ**

  አፈታሪክ ባለፈ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚነገር ስሆን በአብዛኛው በአንድ በተወሰነ አካባቢ ከተፈፀመ እውነተኛ ታሪክ አንድ ገፅታ በመውሰድ ስነቃላዊ ፈጠራ ተጨምሮበት የሚነገር ነው፡፡ የአፈታሪክ አላማ አንዳንድ አሳሳቢ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ እንዲሁም አፈታሪክ የሚነገርበት መሰረታዊ ምክንያት ለተዝናኖት ሳይሆን ሰዎችን ለማስተማር ነው፤ አንድን አስፈላጊ ጉዳይ እንዲያውቁ ለማድረግና በባህላቸው የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል ዝግጁ እንዲሆኑ ለማስጠንቀቅ ነው፡፡

ለ/ በአዲስ አበባ "እሪ በከንቱ" የተባለው ሰፈር እንዴት ተሰየመ? ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል ያገኛችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአየር ንብረት ምንነትና ለውጦች የሚያስከትሉትን ችግር አይተናል፡፡ በመቀጠል መልካሙን ነገር እንፈፅም የሚለውን ፅሁፍ የተመለከትን ሲሆን ከዚያም በኢትዮጵያ ካርታ ውስጥ ኦሮሚያ ክልልን የሚያዋስኑ ክልሎችን አይተናል፡፡

ከዚም ውጥን ታሪኮችን አሟልቶ መፃፍን ያየን ስሆን ለመዝገበ ቃል ፍቺም ሰጥተናል፡፡

እናም ከሐረግ አይነቶች አንዱ የሆነውን ግሳዊ ሐረግን በምሳሌ በማስደገፍ የተመለከትን ስሆን “ባሏ የሞተባት ሴት” በሚል የቀረበን ተረት ያየን ስሆን በስተመጨረሻም የአፈተሪክን ምንነት ተመልክተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት እንደሚከሰት ዘርዝሩ።
2. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንት የሚከሰቱ ችግሮችን ዘርዝሩ።
3. ኦሮሚያ ክልልን የሚያዋስኑ ክልሎችን ዘርዝሩ።
4. ከተለያዩ የሐረግ አይነቶች የግሳዊ ሐረግን ተግባር በምሳሌ አሳዩ።
5. የአፈታሪክን ምንነት ግለፁ።

❖ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ፍቻቸውን ስጡ።

1. ማፌዝ
2. ሾተል
3. ቁርኝት
4. መሰናክል
5. ሀቅ
6. ህያው
7. መኖ
8. ማደራጀት
9. ቁንጮ
10. ሸለለ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅፅ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት ትምህርት ምን ያህል እንደ ተረዳችሁ የሚታመሳከሩበት ቅፅ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ( ) እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ( ?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| | የማመሳከሪያ ነጥብ | ✓ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ አየር ንብረት የቀረበውን ምንባብ ይዘት መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የኦሮሚያ ክልልን የሚያዋስኑ ክልሎችን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በውጥን የቀረበ ታሪክን አሟልቶ መፃፍ ሂደትን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላት ፍቺ መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የግሳዊ ሐረግ ምንነትና ተግባር መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የአፈታሪክ ምንነትን ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |

ከዚህ በላይ በቀረበው ቅፅ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

## ዋቢ መፃሕፍት


- ብርሃኑ ገበየሁ። (1992)። የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ስብስብ። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።
- ---------------። (1999)። የአማርኛ ስነ-ግጥም። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።
- ብርሃኑ ገ/ፃድቅ። (2000)። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምሪያ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።
- ባየ ይማም። (2002)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋሰው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።
- አዲሱ ያለው። (2008)። ዘመናዊ የአማርኛ መፅሐፍ ሶስት።
- ዘሪሁን አስፋው። (1995)። የልቦለድ አዋጅ እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።
- -----------------። (2002)። የስነፅሁፍ መሰረታውያን። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።
- ጌታሁን አማረ። (1990)። ዘመናዊ የአማርኛ በቀላል አቀራረብ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

- (http://www.mor.gov.et/ የገቢዎች ሚንስቴር ደህረ-ገፅ።)
- ANRS: Environoment, Forest, and Wild Life Protection and Development Authority

| ቃላት ከነፍቻቸው | |
|---|---|
| ቃላት | ፍቻቸው |
| • ደህንነት- | ሰላም |
| • የተቆራኙ- | የተገኘ |
| • አያሌ | ብዙ |
| • ምቹ | የተደላደለ |
| • ቁራጭ | ጥቂት |
| • ማዛባት | ቅደምተከተሉን ያልጠበቀ |
| • ማስወገድ | ማጥፋት |
| • ውስን | የተገደበ |
| • ክዋኔ | ድርጊት ወይም ተግባር |
| • መገለጫ | ማሳያ ወይም መታወቂያ |
| • እንብርት | የሰውነት ክፍል |
| • አስተዋፅኦ | አበርክቶ |
| • ማበላለጥ | ማዳላት |
| • ወዳጅ | ዘመድ |
| • አዛባ | የከብት ፍግ |
| • ጠላት | ደመኛ |
| • ተወቃሪ | አንድነት፣ አንድ አካል |

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም